# ዜና መጽሔት
ቁ.19



# NEWSLETTER

Volume 19 July 2021

046-220-53-11
046-220-82-52
046-220-46-26
Fax: 046 220-49-75

P.O.Box 05
www.hu.edu.et
Email: info@hu.edu.et

Office of External Relations & Communications, OERC
Public Relations & Communications Directorate, PRCD

ሁሌም ለልህቀት!

Ever to Excel !



## ተልዕኮ

ጥራትና አግባብነት ያለዉን ትምህርትና ስልጠና፣ ምርምር፣ የማህበረሰብ አገልግሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማካሄድ ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃንን ማፍራትና ማህበረሰቡን ማገልገል::

## ራዕይ

በ2022 ዓ.ም ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ከሚገኙ ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሆኖ መገኘት::

## እሴቶች

ልህቀት፣ ጥራት፣ ቁርጠኝነት፣ አቃፊነት፣ ትብብር፣ ዓለም ዓቀፋዊነት::

# Newsletter

Volume 19 July 2021

**Editors-in-chief**
Mathewos W.Giorgis (Asst/Prof.)

**Co-editor & Writer**
Sileshi Negash

**Reporters**
Dawit Bedasa
Tesfaye T/Mariam
Tadios Abide

**Graphics Designer**
Yididiya Simon 0915 6711 76

**Photographer**
Haile Beyi

**Contributors**
Professionals from Departments of ELL, JC & SAL

**Marketing & Promotion**
Birukt Chaka

**Driver**
Birru Taramo

**Printing Press**
Sheger Printing Press

# ማውጫ | Table of Contents


1. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የእውቅና ሽልማት ዋንጫ ተበረከተለት.................. 6
2. የተፈጥሮና ኮምፒዩቴሽናል ሳይንስ ኮሌጅ የተለያዩ የምክክር መድረኮችን አዘጋጀ.............................. 7
3. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት.. 9
4. የአዋዳ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የጥራት ማረጋገጫና ማሻሻያ ሥልጠና ሰጠ............................ 10
5. የኖርዌይ ኢምባሲ የአየር ንብረት እና የደን አማካሪ በወንዶገነት ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ ጉብኝት አካሄዱ.......................................................................................................................... 11
6. በመንገዱ ዘርፍ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ተካሄደ............. 12
7. የተፈጥሮና ኮምፒዩቲሽናል ሳይንስ ኮሌጅ የእንስሳት ህክምና ፋካሊቲ የእንስሳት ህክምና ማስተማርያ ሆስፒታል አስመረቀ..................................................................................................... 13
8. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ቤነፊት ሪያላይዝ ፕሮጀክት ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ አዘጋጀ... 14
9. የጂኦግራፊና አከባቢ ጥናት ትምህርት ክፍል ውጫዊ የስርዓተ ትምህርት ግምገማ አካሄደ................. 15
10. ለዩኒቨርሲቲዎችና ምርምር ተቋማት ስነ-ምግባር ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተሰጠ.......................................................................................................................... 16
11. ትምህርት ኮሌጅ በሳይንሳዊ የወረቀት አፃፃፍ ክህሎት ላይ ስልጠና አካሄደ.......................................... 17
12. የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ስትራቴጂክ ዕቅድ አዘገጃጀት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና አዘጋጀ.... 18
13. የተለያዩ ኮሌጆች ዓመታዊ የምርምር ግምገማ አካሄደ............................................................................. 19
14. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ የዓለም የሴቶች ቀንን አከበረ.......................................................... 21
15. የወንዶ ገነት ደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ እና ጂኦ ፋሻል ኢንፎርሜሽን ሴንተር በተለያዩ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ዙሪያ በጋራ ለመስራት ተስማሙ ................................................................. 22
16. በምር/ቴክ/ሽግ/ም/ፕ/ጽ/ቤት የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በሲዳማ ክልል ወንዶገነት ወረዳ ለሚገኙ አርሶ አደሮች ምርጥ ዘሮችን አበረከተ........................................................................... 23
17. በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በእምቦጭ መጤ አረምና ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ የምክክር አውደ ጥናት ተካሄደ 24
18. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የማህበርሰብ አግልግሎት ዳይሬክቶሬት የአካባቢውን ማህበረሰብ ትኩረት ያደረጉ በርካታ ተግባራትን አከናወነ.................................................................................................... 25
19. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ መራሒት ክበብ በሴት ተማሪዎች ዙሪያ ልዩ ፕሮግራም አዘጋጀ.......................... 27
20. የሳይንስና ቴክኖሎጂ እና ምንድስና ማዕከል በሮቦቲክስ ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች አስመረቀ.......... 28
21. የስነምግባርና ጸረ-ሙስና መከታተያ ዳይሬክቶሬት የተማሪዎች ጥያቄና መልስ ውድድር አካሄደ......... 29
22. ግብርና ኮሌጅ በከብቶች ላይ እየሠራ በሚገኘው ምርምር ዙሪያ ገለጻ ከማድረጉ ባሻገር የመስክ ጉብኝት አካሄደ.......................................................................................................................... 30
23. የ6ኛው ሀገራዊ ብሔራዊ ምርጫ ሂደት ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ምቹ አውድ ከመፍጠር አንፃር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚና የላቀ መሆኑ ተገለጸ........................................ 31
24. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ጋር በመሆን ለሚመለከታቸው ' ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ስልጠና ሰጠ............................................................................................. 32
25. ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተለያዩ ተግባራትን አከናወነ........................................................ 33

26. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የጆርናል ስርዓት መተግበሪያ ሶፍትዌር ይፋ አደረገ........ 35
27. የተፈጥሮና ኮምፒቲሽናል ሳይንስ ኮሌጅ ሁለተኛውን ሀገር አቀፍ የምርምር ኮንፈረንስ አካሄደ........ 36
28. በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የወንዶ ገነት ደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ ሶስት የ3ኛ ድግሪ ፕሮግራሞችን ለመክፈት በባለሙያዎች አስገመገመ........ 37
29. የትምህርት ኮሌጅ የ2013 ዓ.ም ዕጩ ሴት መምህራን ከአንጋፋ ሴት መምህራን ጋር የልምድ ልውውጥ እንዲያደረጉ የምክክር መድረክ አዘጋጀ........ 38
30. የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሲዳማ ጥናት ተቋም በሀገር በቀል ዕውቀቶች ላይ ሲያደርግ በነበረው ምርምር ዙሪያ የምክክር መድረክ አዘጋጀ........ 39
31. የማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ የጥራት ማረጋገጫ መሰረታዊን እና ፕሮግራም ምዘና ላይ ስልጠና ሰጠ........ 40
32. ስራ አጥ ወጣቶች ተደራጅተው በዶሮ እርባታ ስራዎች እንዲሰማሩ ተደረገ........ 41
33. ክብርት ዶ/ር ሂሩት ካሳው በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ችግኝ ተከላ አካሄዱ........ 42
34. የሰላም ሚኒስቴር የብሔራዊ የበጎ ፈቃድ ማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራም ሂደት ስኬትን በማስመልከት የዕውቅና አሰጣጥ መድረክ አዘጋጀ........ 43
35. College of Law and Governance Hosts National Research Conference........ 44
36. Hawassa University hosts Ethiopian Premier League Matches........ 45
37. Institute of Technology hosts a Third National Conference on Aspiring the Future in Engineering and Technology........ 46
38. Hawassa University Goes into a Memorandum of Understanding with NGDO Catalan Association for Cooperation Sport Development and Education.. 47
39. Hawassa University Hosts National Conference on Enhancing Reading Culture for Quality Education and Research........ 48
40. College of Natural and Computational Science Hosts Third National Research Conference........ 49
41. College of Agriculture Conducts an Internal Curriculum Review Workshop... 50
42. Hawassa University, Indian Embassy in Collaboration Celebrate International Yoga Day........ 51

# የዝግጅት ክፍሉ መልዕክት | Editorial |

ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከቀደምት ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በመጀመሪያዎቹ ተርታ የሚገኝ ሲሆን በመማር ማስተማር፣ በጥናትና ምርምር፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ ሽግግርና በማህበረሰብ አገልግሎት አመርቂ ውጤት የሚያሳዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። ዜጋን በዕውቀት እያስታጠቀ በክህሎት የዳበረ እና በሥነ ምግባር የታነጸ ትውልድን ለመፍጠር የበኩሉን አስተዋፅዖ እያበረከተ ያለ ዩኒቨርሲቲ ነው።

ለሁለንተናዊ ዕድገት ደግሞ ሰላም ወሳኝ ሚና እንዳለው በማመን ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መቀራረብ ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል። ይህን ዓላማ ከዳር ለማድረስ ሲባል የተሳለጠ ተግባቦት እንዲኖር የሕዝብ ግንኙነቱ ሥራ እንዲጠናከር የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል። ከሕዝብ ግንኙነቱ ተግባር አንዱ በዩኒቨርሲቲው በየደረጃው የሚገኙ የመዋቅር አካል ክፍሎች የሚከውኑትን የተለያዩ ተግባራት የሚዲያ ሽፋን ከመስጠት ባሻገር በህትመት መረጃ የሚሰራጭበትን ሥራ ይሠራል። በመሆኑም የተግባቦት ዳርቻውን ለማስፋት በተለያዩ ጊዜያት የተከናወኑ የተለያዩ የሥራ ክፍሎችና ኮሌጆች ተግባራት የሚያሳዩ ዜናዎችን የያዘች መጽሔት ለንባብ ሲያበቃ መልካም ንባብን ይመኛል።

As one of the first generation universities in Ethiopia, HU has the vision to be a top-ranking university in East Africa. So as to objectively achieve goals for such a vision, the communications aspect should play a vital role in accumulating and leading up the effort to organize and disseminate relevant information to partners and HU community in a quality, in number, and in time.

With this, indeed, the directorate (PRCD) believes that all level administrative bodies of HU, as well as internal and external communities, should have a better understanding of the essentiality of communications in a wider context. We hope this newsletter can inform you what has been done under different administrative structure levels. Therefore, we wish you all enjoy it and expect your suggestion for further steps.

The Director,

July 2021

# የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የእውቅና ሽልማት ዋንጫ ተበረከተለት

በስለሺ ነጋሽ





የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ላለፉት 40 ዓመታት በመማር ማስተማር፣ በምርምርና ተክኖሎጂ ሽግግር እና በማህበረሰብ አገልግሎት ላበረከተው አስተዋጾዎ ከኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የእውቅና ሽልማት ተበርክቶለታል፡፡

ዶ/ር ዮሐንስ በንቲ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ፕሬዝዳንት ዩኒቨርሲቲው በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት አንጋፋ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ መሆኑን ገልጸው ላለፉት በርካታ ዓመታት በርካታ ምሁራኖችን በማፍራትና ለትምህርት ማህበረሰቡ እያበረከተ ያለውን አስተዋፅዖ በመገንዘብ በኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ስም የእውቅና ሽልማት ልናበረክትላችሁ በመገኘታችን ደስታችንን እየገለጽን ሀገር መቀየርና ለውጥ ማምጣት የምንችለው በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን በአግባቡ በማስተማርና በስነ-ምግባር በማነጽ በመሆኑ በርትታችሁ እንድትሰሩ አደራ እያልኩኝ ከሳይንስና ከፍተኛ ሚኒስቴር ጋርም በመተባበር አስፈላጊውን ድጋፍ እናደርጋለን ብለዋል፡፡

ኢንጅነር ቢኒያም አለማየሁ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በ4382 ካሬ ላይ ባለ32 ፎቅ ሁለገብ ህንጻ በአዲስ አበባ ሰንጋ ተራ አካባቢ ሊገነባ ዝግጅቱን ማጠናቀቁንና ህንጻው ሙዚዬምን፣ ባንኮችን፣ ቢሮዎችን እና አዳራሾችን በውስጡ የያዘ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር አያኖ በራሶ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው ላለፉት ዓመታት የሰራቸውን ስራዎች ገምግሞ ማህበሩ የእውቅና ሽልማት ስላበረከተልን እያመሰገንኩ፤ በተደረገልን ሽልማትና ማህበሩ በአዲስ አበባ ተምሳሌት የሚሆን እና በዓለም ደረጃ እይታውን ከፍ የሚያደርግ ህንጻ ሊሰራ በመሆኑ የተሰማኝንም ደስታ እየገለጽኩኝ ሽልማቱ ወደፊት ተግተን እንድንሰራ የሚያበረታታን በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ህንጻው ተገንብቶ እስከሚያልቅ በመደገፍ ከጎናችሁ እንደሚቆም ለማሳወቅ እወዳለሁ ብለዋል፡፡



# የተፈጥሮና ኮምፒዩቴሽናል ሳይንስ ኮሌጅ የተለያዩ የምክክር መድረኮችን አዘጋጀ

በስለሺ ነጋሽ







## በዓሳ ሀብት ዙሪያ የተዘጋጀ የምክክር መድረክ

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮና ኮምፒዩቴሽናል ሳይንስ ኮሌጅ በአኳ ካልቸርና በዓሳ ሀብት ዙሪያ ከደቡብና ሲዳማ ክልል ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ባዘጋጀበት ወቅት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር አያኖ በራሶ የውሃ ሀብት ለመጠቀም መነሻ ሃሳቦችንና ምርምሮችን በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በመጀመር አኳ ካልቸርና የዓሳ ሀብትንም ለማበልጸግ በትምህርት መደገፍ ስላለበት በዚህ ዙሪያ ከመጀመሪያ እስከ ሶስተኛ ድግሪ በማስተማር ላይ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ትናንሽ ኩሬዎችን በማዘጋጀትና ዓሳን በማምረት ዓሳ ለገቢ ምንጭ፣ ለምግብ እና ለስራ ፈጠራ ማዋል እንደሚቻል ለህብረተሰቡና ለአርሶ አደሩ ሰርቶ ማሳያ አኳ ካልቸር ማዕከል መዘጋጀቱንና ወደፊትም ዩኒቨርሲቲው በዘርፉ የልህቀት ማዕከል እንደሚሆን ተናግረዋል፡፡

ተመራማሪና የአኳ ካልቸር ማዕከል ኃላፊ ዶ/ር ካሳዬ ባልከው  እንደገለጹት እስካሁን በዘርፉ አኳ ካልቸር አዲስ በመሆኑ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠቱን፣ ለአርሶ አደሩም እንደግብዓት የሚፈልጋቸውን የዓሳ ዝርያዎች በማከፋፈል ውጤቱ ምን እንደሚመስል ግብረ መልስ በመውሰድ ውጤታማ መሆኑንና የአኳ ካልቸር ግብዓቶችን በመስጠትና በማማከር  ዙሪያ በዩኒቨርሲቲው እየተሰራ ይገኛል፡፡

የመድረኩ ተሳታፊ የሆኑት የሀዋሳ ሃይቅ የዓሳ አስጋሪዎች ማኅበር ኃላፊ አቶ ዳዊት አብርሃምም በበኩላቸው የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሀዋሳ ሀይቅ በጎርፍና በደለል መሞላቱን፣ በዙሪያው ላይ የእርሻ መስፋፋት እንዳለ እና ከኢንዱስትሪ የሚለቀቁ ፈሳሾች ሃይቁን እየጎዱት መሆኑን በጥናት በማስቀመጥ ሃይቁንና በውስጡ ያሉትን ብዝሃ ሀብቶች ለመታደግ በርካታ ስራዎችን እየሰራ መሆኑን ገልጸው የማህበሩ አባላት ከዚህ መድረክ የተለያዩ ኩሬዎችን በማዘጋጀት ዓሳን ማምረት እንደሚቻልና ለሀይቁም የእፎይታ ጊዜ መስጠት እንደሚቻል ግንዛቤ ያገኙበታል ብለዋል፡፡



## “በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያስተምሩ ሴት መምህራንን በሳይንስ፣ በምርምር እና መሪነት ዙሪያ ማብቃት” በሚል ርዕስ የተዘጋጀ የምክክር አውደ ርዕይ





የኮሌጁ ዲን ዶ/ር ዘይቱ በጋሻው የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ ሲገልጹ አዲስ የተቀጠሩት መመህራን ከነባሮቹ መመህራን የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ፣ ሴቶች በሳይንስ፣ በምርምር እና በአመራር ደረጃ እራሳቸውን ማብቃት እንዲችሉና በሚያጋጥማቸው ችግሮቻቸውና መፍትሄዎቻቸው ላይ ምክክር ለማድረግ ነው ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በኮሌጁ ሴት መምህራንን በዝውውር፣ በቅጥርና አብላጫ ውጤት ያመጡ ተመራቂዎችን በማወዳደርና በመቅጠር ከአምስት ዓመት በፊት 5 የነበረው የሴት መምህራን ቁጥር በአሁኑ ሰዓት 53 የደረሰ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በኮሌጁ ባይሎጂካል ሳይንስ ዲን ዶ/ር ዙፋን በደዊ እንደተናገሩት ሴቶች እራሳቸውን ለማብቃት ትስስር መፍጠር፣ በየጊዜው በመገናኘት ምክክርና ውይይት ማድረግ፣ ውድድር መፍጠርና ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሄዎችን ለማምጣት አንድነትና መተባበር ያስፈልጋቸዋል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የቴክ/ሽግግር አስተባባሪ መምህርት ስመኝ ሰርካ የሴት መመህራኖቻችን ቁጥር ከበፊቱ እየጨመረ የመጣ ሲሆን ነባር መምህራን ለአዲሶቹ አርአያ በመሆንና ከመደበኛው የገጽ ለገጽ ውይይት በተጨማሪ ቴክኖሎጂ የፈጠረልንን አጋጣሚ በመጠቀም ኢ-መደበኛ ትስስር ሊመሰረት ይገባል ብለዋል፡፡



# የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የምርምርና ማህበረሰብአገልግሎት ዳይሬክቶሬት

በሀዋሳ ከተማ ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ሴት ተማሪዎች ስልጠና የሰጠ ሲሆን በሌላ ዜና ደግሞ የምርምር ቀን አክብሯል፡፡

ቅንብሩ በሕግኮዳ

## ለሴት ተማሪዎች ስልጠና ሰጠ

ዳይሬክቶሬቱ ከ40 ለሚበልጡ ሴት ተማሪዎች ስልጠና የሰጠው ከሀዋሳ ከተማ ትምህርት መምሪያ ጋር በመተባበር "**ጤና ለአንድ ሴት ተማሪ**" በሚል መሪ ቃል ሲሆን የዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር ረ/ፕሮፌሰር አለሙ ጣሚሶ የከተማችንን ሴት ተማሪዎች ለማብቃት እንዲሁም ተሳትፎአቸውንና ተጠቃሚነታቸውን በሁሉም ዘርፍ ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወኑ መሆናቸዉን ጠቅሰዉ ሴት ተማሪዎቻችን በትምህርታቸው ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ሕይወታቸውን በክህሎትና በጥበብ እንዲመሩ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡ አክለውም ስልጠና የወሰዱ ተማሪዎች በቆይታቸው ያገኙትን እውቀት ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉና ለትምህርታቸው ብቻ ትኩረት በመስጠት ከዚህ በኋላ የሚኖረው ሕይወታቸው የተማሩትን መምሰል ይገባዋል ብለዋል፡፡







## የምርምር ቀንን አከበረ

የምርምር ቀን በኮሌጁ በተከበረበት ዕለት ለማወቅ እንደተቻለው አስር የምርምር ውጤቶች ለባለድርሻ አካላት ለውይይት ቀርበዋል፡፡ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ አለሙ ጣሚሶ (ረ/ፐ) የፕሮግራሙ ዓላማ የኮሮና ወረርሽኝ ከተከሰተ ጀምሮ የተሰሩ የምርምር ውጤቶች ለማህበረሰቡ አቅርቦ ውይይት ማድረግና የምርምር ቀን ማክበር በማስፈለጉ ይህ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ብልጫ ላስመዘገቡ መምህራንና ተመራማሪዎች የእውቅና ሽልማት ለመስጠት መቻሉን ገልጸዋል፡፡

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደርና ተማሪዎች አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሳይ ሀይሉ በበኩላቸው የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ አንዱ ተልዕኮ የምርምር ውጤቶችን ለህብረተሰቡ ተደራሽና ተግባራዊ ማድረግ መሆኑን ገልጸው በዕለቱ የቀረቡት የምርምር ስራዎች ለዓለም ጤና ስጋት በሆነው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ላይ በመሆኑ ህብረተሰቡ ስለ ወረርሽኙ ያለውን ግንዛቤ ለመረዳትና ለማሳደግ፣ ለሳይንሱ ማህበረሰብ ተጨማሪ ምርምሮችን እንዲሰሩ፣ የተሰሩ ስራዎች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ለመገምገም፣ ለመማር ማስተማሩ ምን አስተዋፅዖ እንዳበረከቱ እንዲሁም ተጨማሪ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች አቅጣጫ ለማስቀመጥ ይረዳል ብለዋል፡፡





# የአዋዳ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የጥራት ማረጋገጫና ማሻሻያ ሥልጠና ሰጠ

ኮሌጁ (ኤዲትንግ - ሕግኮዳ)

ኮሌጁ ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የጥራት ማረጋገጫና ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር ለትምህርት ክፍል ሃላፊዎችና የጥራት ማረጋገጫና ማሻሻያ አስተባባሪዎች ስልጠና በአዋዳ ካምፓስ ስልጠና ሰጥቷል፡፡

የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኮሌጁ ዲን ዶ/ር ወገኔ ማርቆስ በትምህርት ክፍል አስተባባሪዎች መካካል ባለው ክፍተት እና የተደራጀ የመስሪያ ሰነድ ያለመኖር የትምህርት ጥራቱን በተፈለገው ደረጃ ለማረጋገጥ ችግር ሆኖ መቆየቱንና ለዚህም አስፈላጊው ሰነድ የተዘጋጀበት ይህ ስልጠና ክፍተቱን ለመሙላት ትልቅ አቅም እንደሚሆን ገልጸው የትምህርት ክፍል ሃላፊዎችና አስተባባሪዎች ለትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ አሰሳሰበዋል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የጥራት ማረጋገጫ እና ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተወካይ መቅደስ መኮንን በበኩላቸው የትምህርት ጥራት የአንድ ወቅት ስራ አለመሆኑን አውስተው ለዚህም ኮሌጁ ተከታታይ ክትትል እንዲያደርግ በማሳሰብ ዳይሬክቶሬታቸው አስፈላጊዉን ድጋፍ እንደሚያደርግ ቃል ገብተዋል፡፡

ስልጠናው ሁለት መርሐ ግብሮችን ያካተተ ሲሆን በመጀመሪያ የትምህርት ክፍል የጥራት ማረጋገጫ እና ማሻሻያ አስተባባሪዎች ሃላፊነትና ተግባር በተመለከተ እና በማስከተልም የኮሌጁ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ እና ማሻሻያ ሰነድ አስመልክቶ የቀረበ ስልጠና መሆኑ ታውቋል፡፡ በስልጠናውም ከ20 በላይ ታዳሚዎች ተሳትፈዋል፡፡





# የኖርዌይ ኢምባሲ የአየር ንብረት እና የደን አማካሪ በወንዶገነት ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ ጉብኝት አካሄዱ

በሕግኮዳ



ሚሲስ ማሪ ማርቲሰን ከጎብኚ ቡድን ጋር ጉብኝታቸውን ባካሄዱበት ወቅት የኮሌጁ ዲን ዶ/ር ሞቱማ ቶሌራ፣ የ**MRV (National Measuring Reporting and verification)** ፕሮጀክት አስተባባሪ ዶ/ር አብደላ ጉሬን ጨምሮ ሌሎች የኮሌጁ አመራሮችና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ መንግስት የRedd+ (Plus) ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ተሻለ ወ/ማርያም በስፍራው በመገኘት እንግዶችን እንኳን ደህና መጣችሁ ብለዋል፡፡

ቡድኑ ጉብኝቱን በ**MRV** ፕሮጀክት ሥር የሚደገፉ የሁለተኛ ዲግሪ (MSc) ተማሪዎች የሚገለገሉበትን ላብራቶሪ በመመልከት የጀመረ ሲሆን ይህ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ኖርዌይ ኢምባሲ የሚደገፍ ሆኖ ጅማሬውም እ.ኤ.አ ታህሳስ 2014 ዓ.ም ሆኖ ማብቂያው እ.ኤ.አ ጥር 2021 ዓ.ም ቢሆንም ነገር ግን በኮቪድ-19 መከሰት እና ሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች የተነሳ የታለመለትን ዓላማ ባለማሳካቱ እስከ ነሐሴ 2021 ድረስ የተራዘመ መሆኑ ታውቋል፡፡

ኮሌጁ በሀገር ውስጥና ከሃገር ውጭ በስፋት የሚታወቅበትን ውብ እና ማራኪ የተፈጥሮ ደን ተዘዋውረው በተመለከቱበት ወቅት በእፅዋቶቹ ላይ ምርምር እያደረጉ ያሉ መምህራን ለጎብኚ ቡድኑ ሰፊ ማብራርያና ገለፃ አድርግዋል፡፡ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ነገሌ አርሲ ወረዳ ገበታ አርጃ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ የሚገኘውን የግራር ደን ሳይት ለመመልከት በተገኙበት ወቅት ገለፃ ያደረጉት የኮሌጁ ዲን ዶ/ር ሞቱማ ቶሌራ የምርምር ሳይቱ እ.ኤ.አ በ2006 ዓ.ም በኮሌጁ በጀት የተጀመረ መሆኑን ጠቅሰው ነገር ግን በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ በሚዘወተረው እንጨቶችን ለማገዶነት የመጠቀምና ከብቶችን ለግጦሽ ማሰማራት የተነሳ ደኑ ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑን ገልጸዋል፡፡



# በመንገዱ ዘርፍ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ተካሄደ

በአድኖ ማርቆስ

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አዘጋጅነት ከኢትዮጵያ መንገዶች ባልስልጣንና ከተለያዩ የዩኒቨርሲቲ ተቋማት የተውጣጡ ምሁራን በመንገዱ ዘርፍ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ በሀዋሳ ከተማ ውይይት አካሂደዋል፡፡ በውይይቱ ላይ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከፍተኛ ሀላፊዎችን ጨምሮ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ኢንስትቲዩት፣ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ የጅማ ዩኒቨርሲቲ እና የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን የተገኙ ሲሆን ከእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲዎች ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡ ፡ ምሁራኑ በጥናታቸውም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ቀና ትብብርና ያላሰለሰ ድጋፍ መኖር፣ የአስተማሪዎች ጥረትና ተነሳሽነት መኖር፣ ለምርቃት የበቁት ተማሪዎች በሙያቸው የበቁ ሆኖ መውጣት የነበሩ ጠንካራ ጎኖች ሆነው ተነስተዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የኮርፖሬት አገልግሎት ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ በቀለ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ከተጠቀሱት 7 ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ውል በመፈራረም የተማሪዎችን ሙሉ ወጭ በመሸፈን በተለያዩ የምህንድስና ሙያ ዘርፎች ተማሪዎችን በማስተርስ ፕሮግራም በማሰልጠን ላይ እንደሚገኝ አብራርተው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በዘንድሮው ዓመት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙትን ጨምሮ በጥቅሉ የ5 ሺህ ተማሪዎችን ሙሉ ወጪ በመሸፈን እንዲሰለጥኑ አድርጓል ነው ያሉት፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ባለፉት አሥርት ዓመታት ላሰለጠናቸው ተማሪዎች ከ377 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ማድረጉን አስታውቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በዘርፉ የሚያጋጥመውን ብቁ የሰው ኃይል እጥረት በመቅረፍና ዘርፉን በማዘመን አወንታዊ ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ ረገድ አስተዋፅዖው ከፍተኛ መሆኑ በግምገማው የተመላከተ ሲሆን ከሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡት ምሁራን በበኩላቸው ምህንድስና ለመንገዱ ዘርፍ ብሎም ለሀገር እድገት ሚናው የማይተካ መሆኑን በማንሳት በዘርፉ የበቁ ባለሙያዎችን ለማፍራት በትብብር እንደሚሰሩ አረጋግጠዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በዩኒቨርሲቲዎች ዘርፉን ለማሳደግ  ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ያረጋገጠ ሲሆን በውይይቱ መጨረሻም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥምረታቸውን አጠናክረው በማስቀጠል ካለፈው በላቀ ሁኔታ መሥራት በሚያስችሏቸው ጉዳዮች ዙሪያ አቅጣጫዎችን አስቀምጠዋል፡፡





# የተፈጥሮና ኮምፒዩቲሽናል ሳይንስ ኮሌጅ የእንስሳት ህክምና ፋካሊቲ የእንስሳት ህክምና ማስተማርያ ሆስፒታል አስመረቀ

በተስፋዬ ተ/ማ (ኤዲትንግ በሕግኮዳ)

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮና ኮምፒዩቲሽናል ሳይንስ ኮሌጅ የእንስሳት ህክምና ፋካሊቲ የእንስሳት ህክምና ማስተማርያ ሆስፒታል ሲያስመርቅ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር አያኖ በራሶ ዩኒቨርሲቲው በሀገራችን ውስጥ ከሚገኙ የመንግስት አንጋፋ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ መሆኑንና በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በቴክኖሎጂ ሽግግሩ ዘርፍ ትልቅ ለውጥ እያስመዘገበ በመሆኑ በሀገራችን በእንስሳት ህክምና ዘርፍ ያለውን የተማረ የሰው ኃይል እጥረት በመቀነስ ረገድ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ልዩ ትኩረት ሰጥቶና ከፍተኛ በጀት መድቦ የእንስሳት ህክምና ማስተማርያ ሆስፒታል ያስገነባ መሆኑን ገልጸዋል። አያይዘውም ዩኒቨርሲቲው የእንስሳት ግጦሽና የእንስሳት ፋካሊቲን በአንድነት አቀናጅቶ ኮሌጅ የማድረግ እቅድ እንዳለው ጠቁመው ሆስፒታሉ አዲስ ከመሆኑም ጋር ተያይዞ መሟላት ያለባቸውንና በጨረታ ሂደት መጓተትም ሆነ በተለያየ ምክንያት እስካሁን ያልተሟሉ እቃዎችን በፍጥነት ለሟሟላት ቃል የገቡ ሲሆን ሆስፒታሉ የተገነባው ለማህበረሰቡ ግልጋሎት ለመስጠት ስለሆነ ህብረተሰቡ እንደ እራሱ ንብረት በማየት አስፈላጊውን ጥበቃ እንዲያደርግለት ጥሪ አቅርበዋል።

የኮሌጁ ዲን ዶ/ር ዘይቱ ጋሻው በበኩላቸው በኮሌጁ ተመራማሪዎች አማካኝነትም ለሀገር ፋይዳ ያላቸው ምርምሮች እየተካሄዱ መሆኑንና ሆስፒታሉ መገንባቱ ምርምራቸውን በብዙ እንደሚደግፍ ገልጸዋል። ይህም ከዚህ በፊት ለምርምር ስራ እስከ አርሲ ነጌለ ድረስ የሚደረገውን ጉዞ ያስቀራል ያሉ ሲሆን ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ፕሮፌሰሮች ከዚህ በፊት በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ዙሪያ በሲዳማ ክልል በመዘዋወር ያለውን አቅም ምልከታ ማድረጋቸውን አውስተዋል። ዩኒቨርሲቲዎች የፌዴራል መንግስት ተቋማት እንደመሆናቸው መጠን እስከ ቦረናና ጅግጅጋ ድረስ አገልግሎት ይሰጣል ብለዋል።

መምህር እና ተመራማሪ ፕሮፌሰር ካሳሁን አስማረ የእንስሳት ህክምና ትምህርት ክፍል ከዛሬ 18 ዓመት በፊት መጀመሩንና በአሁኑ ወቅት ደግሞ ወደ ፋካሊቲ ደረጃ መሸጋገሩን የገለጹ ሲሆን የሆስፒታሉ መከፈት በእውቀትና በስነምግባር የበቁ ባለሙያዎችን በማፍራት ሀገሪቱ ከዚህ ዘርፍ ተጠቃሚ እንድትሆን ያደርጋታል ብለዋል። ባሁኑ ጊዜም ፋካሊቲው በሀገር አቀፍ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና በቂ ውጤት ያመጡትንና በዲፕሎማ ሁለት ነጥብና ከዚያ በላይ ያላቸውን ተማሪዎች በመቀበል በመጀመሪያ ዲግሪና በሁለተኛ ዲግሪ እያስተማረ እንደሚገኝ ገልጸው ለመንግስት መስሪያ ቤቶችም ሙያዊ ድጋፍን ለመስጠት በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

በመጨረሻም የሲዳማ ክልልን፣ የሀዋሳ ከተማ አስተዳደርን፣ እንዲሁም የቱላ ክፍለ ከተማንና የጨፌ ኮቲ ጀቤሳ ቀበሌን ወክለው በስነስርዓቱ ላይ የተሳተፉ የዘርፉ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የህብረተሰብ ክፍሎች የሆስፒታሉ መገንባት አይነተኛ ሚና እንዳለው ገልፀው በሚያስፈልገው ሁሉ ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።





# የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ቤነፊት ሪያላይዝ ፕሮጀክት ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ አዘጋጀ

በስለሺ ነጋሽ



የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ቤነፊት ሪያላይዝ ፕሮጀክት ባከናወናቸው የተለያዩ ስራዎች ዙሪያ እና የተጠናቀቁ መልካም ተሞክሮዎች በቀጣይ የሚሰፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመምከር በሀዋሳ ሀይሌ ሪዞርት የውይይት መድረክ አዘጋጅቷል። በዚህን ወቅት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር አያኖ በራሶ በፕሮግራሙ መክፈቻ ፕሮጀክቱ በደቡብና ሲዳማ ክልል ላይ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ አስተባባሪነት በ6 ወረዳዎች እንዲሁም በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ አስተባባሪነት ደግሞ በ4 ወረዳዎች ለሚገኙ የሴፍቲኔት ተጠቃሚ አርባ ቀበሌዎች በግብርናው ዘርፍ አርሶ አደሮቹ በምግብ ሰብል ራሳቸውን እንዲችሉ ምርታማ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን የማሳደግ፣ የማላመድና የማሰራጨት ስራዎችን እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

የሀገር አቀፍ ሪያላይዝ ፕሮግራም ኃላፊ ዶ/ር ቴዎድሮስ ተፈራ ፕሮግራሙ በኢትዮጵያ ውስጥ በአምስት ክልሎች ማለትም በትግራይ፣ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ እና ሲዳማ ክልሎች ላይ ዘላቂ የኑሮ ዋስትናን ለማረጋገጥ የምግብ እጥረትን ለመቅረፍ፣ የስርዓተ-ምግብ ችግሮችን ለማስወገድ፣ አካታች እና የስራ ዕድልን በመፍጥር ሴቶችንና ወጣቶችን በማሳተፍና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እና ድጋፎችን በማድረግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ በመሆኑ ውጤቱን በተጨባጭ ለማየት ተችሏል ብለዋል።

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ቤነፊት ሪያላይዝ ክላስተር ኃላፊ ፕ/ር ተስፋዬ አበበ በበኩላቸው ፕሮጀክቱ በደቡብ እና ሲዳማ ክልሎች በቦሎሶ ቦምቤ፣ ዊራና ዊራዲጆ፣ ቃጫቢራ፣ ሻሻጎ፣ ሲልጤ እና በና ዙሪያ ወረዳዎች ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በበቆሎ፣ በሎቅ፣ ገብስ፣ ማሽላ፣ ዳጉሳ፣ ድንች እና ጤፍ ዝርያዎች ላይ እንደስነምህዳሩ አይነት ጥናትና ምርምር በማድረግ የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለአርሶ አደሮቹ እንዲደርሳቸው መደረጉን ገልጸዋል።



# የጂኦግራፊና አከባቢ ጥናት ትምህርት ክፍል ውጫዊ የስርዓተ ትምህርት ግምገማ አካሄደ

በት/ክፍሉ

ዶ/ር ከበደ ተ/ሚካኤል፣ የማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮሌጅ ዲን ተወካይና የኮሌጁ ተባባሪ ዲን በፕሮገራሙ መክፈቻ ላይ ባደረጉት ንግግር በፕሮግራሙ መከፈት እንደ ማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮሌጅ ደስተኛ መሆናቸዉን ከገለጹ በኋላ ት/ክፍሉ ያለውን የሰው ኃይልን ተጠቅሞ የተማረ የሰው ኃይል በማፍራት እና የምርምር ዘርፉን ለማሳደግ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ እና ቁርጠኝነት እንደ ሀገር የተያዘውን የምርምር ዘርፍ ዕድገት ለማሳካት ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳለው ገልፀዋል::

የጂኦግራፊና አከባበቢ ት/ክፍል ኃላፊ የሆኑት ዶ/ር ሙሉእመቤት ወርቁ በበኩላቸው ትምህርት ክፍሉ የትምህርት ስልጠናና የምርምር ዘርፉን ለማሳደግ በቁርጠኝነት እየሰራ እንደሆነ ገለጸዋል:: አያይዘውም ባሁን ሰዓት በአራት የተለያዩ መስኮች ማለትም የውሀ ሀብትና የአየር ንብረት መቋቋም (Water Resource and Climate Change Adaptation)፣ የመሬት ሀብት አስተዳደር (Land Resource Management)፣ ክልላዊና በከተማ ልማት አስተቃቀድ (Regional and Urban Development Planning) እና ጂኦግራፊያዊ መረጃ ዘዴና የካርታ ዝግጅትና ትንተና (Geo-Spatial Planning and Digital Cartography) አዳዲስ ስርዓተ ትመህርት ተቀርጾ አስፈላጊውን ውስጣዊ ግምገማ (internal curriculum review) ሂደት ጨርሰን ወደ ስራ ከመገባቱ በፊት ለውጫዊ (external) የስርዓት ትምህርት ግምገማ የቀረበ መሆኑን አመላክተዋል::



# ለዩኒቨርሲቲዎችና ምርምር ተቋማት ስነ–ምግባር ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተሰጠ

በስለሺ ነጋሽ

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለሀዋሳ ክላስተር ዩኒቨርሲቲዎች፣ ለምርምር ተቋማት እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በምርምር ስነ-ምግባር ዙሪያ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጥቷል፡፡

በመክፈቻ ንግግር ላይ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር አያኖ በራሶ ዩኒቨርሲቲዎችን በተኩረት መስክ እና በተልዕኮቻቸው የመለየት ጥናት በተደረገው መሰረት የምርምር ዩኒቨርሲቲ እንዲሆኑ ከሚጠበቁት ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ዩኒቨርሲቲያችን አንዱ እንደመሆኑ በቀጣይ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ማሟላት ያለበትን መመዘኛ ለማሟላት በአስር ዓመቱ ዕቅዳችን ውስጥ የመጀመሪያ ድግሪ ፕሮግራሞችን በመቀነስ በሁለተኛ እና ሶስተኛ ድግሪ ፕሮግራሞች ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራት መጀመሩን ገልጸዋል፡፡ አክለውም ዩኒቨርሲቲው ችግር ፈቺ ምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ትኩረት በመስጠት በተለይም የአካባቢው ህብረተሰብ የግብርና ምርትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅ፣ የማላመድና የማሰረጨት ተግባር እየተከናወነ ሲሆን የዚህ መሰሉ የምርምር ስነ-ምግባር ስልጠና በመማር ማስተማሩ የትምህርትን ጥራት ከማስጠበቅ እና የምርምር ስራዎቻችን አለም አቀፋዊ እንዲሁም ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ፋይዳው ከፍተኛ ነው ብለዋል፡፡

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሚ/ዲኤታ ፕ/ር አፈወርቅ ካሱ በበኩላቸው የምርምር ስነ-ምግባር ስልጠና ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ እንደተካሄደና ይሄኛውም ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑን አስታውሰው ምርምር ትልቅ ስነ ምግባር የሚፈልግ ተግባር ሲሆን የምርምር ስነምግባር መርሆዎችን ተከትለው የሚሰሩ ምርምሮች ለሀገራችን ችግር ፈቺ ምርምሮችን ከማበርከታቸውም በተጨማሪ በሰው ልጆች፣ በዕጽዋቶች፣ በእንስሳት እና በአጠቃላይ ስነምህዳር ላይ ችግሮች እንዳይከሰቱ በእጅጉ ይረዳናል ብለዋል፡፡



# ትምህርት ኮሌጅ በሳይንሳዊ የወረቀት አፃፃፍ ክህሎት ላይ ስልጠና አካሄደ

በተስፋዬ ተ/ማ (ኤዲትንግ በሕግኮዳ)

ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ኮሌጅ በሳይንሳዊ የወረቀት አፃፃፍ ክህሎት ላይ በዋናው ግቢ ስልጠና በሰጠበት ወቅት የትምህርት ኮሌጁ የትምህርት እና ቴክኖሎጂ ስርፀት ተባባሪ ዲን ዶ/ር ማርቆስ መኩሪያ የትምህርት ኮሌጁ ወደ ኮሌጅ ደረጃ ከማደጉ በፊት ትምህርትና ስልጠና ይባል እንደነበረ ገልፀው ወደ ኮሌጅ ካደገበት ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ በመማር ማስተማሩ፣ በምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም በማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች ላይ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል ብለዋል። አክለውም ኮሌጁ የምርምር ሥራውን ሳይንሳዊና ዓለም አቀፋዊ ለማድረግ በማለም ይህ ስልጠና እንደተዘጋጀ አብራርተው በዚህ ስልጠና ለይ ተሳታፊ የሆኑ መምህራንና ተመራማሪዎች ምርምሮቻቸውን ሳይንሳዊ በማድረግ ረገድ በቂ ክህሎት እንደሚያገኙና በዚህም በርካታ የምርምር ሥራዎችን በውጤታማነት እንደሚያጠናቅቁ ያላቸውን እምነት ገልፀዋል።

የትምህርት ኮሌጅ ዕቅድና ሥራ አመራር አካቶ ዘርፍ ተባባሪ ዲን ዶ/ር አንተነህ ዋሲሁን በበኩላቸው ተሳታፊ ስልጣኞች በኮሌጁ ውስጥ ከሚገኙ አራት ት/ክፍሎች የተውጣጡ መሆኑን ገልፀው ስልጠናው የምርምር ሥራዎቻቸውን በዓለም አቀፍ ደረጃ በማሳተሙ ላይ የሚታየውን ክፍተት ይሞላል ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል።

በመጨረሻም በዕለቱ ስልጠናውን የሰጡት የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ኃላፊ ፕሮፌሰር ተስፋዬ ሰመላ ሲናገሩ በስልጠናው የተሳተፉ መምህራን ከስልጠናው የሚያገኙአቸውን ክህሎቶች በአግባቡ በመጠቀም በሚያከናውኑአቸው ምርምሮች ላይ የተሻለ ውጤታማነትን ሊያመጡ እንደሚገባ ሀሳብ ሰንዝረዋል።





# የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ስትራቴጂክ ዕቅድ አዘገጃጀት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና አዘጋጀ

በማቴዎስ ወ/ጊዮርጊስ

ለተቋሙ ሠራተኞች ግንዛቤ ለማስጨበጥ በወንዲ ገነት ደ/ተ/ሀ/ኮሌጅ የተዘጋጀው ስልጠና በተጀመረበት ወቅት የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሳይንትፊክ ዳይሬክተር ዶ/ር ፋሲካ ቤተ በተማሪዎች ላይ ስንሠራ፣ ምርምር ስናደርግ እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስንሰጥ በዕቅድ መመራት ግድ ይለናል ሲሉ በዘመነ የዕቅድ አዘገጃጀትና ሪፖርት አቀራረብ ክንውኖችን ማሳለጥ እንደሚገባ አስምረውበታል።

ስልጠናውን የሰጡት የፕላንና ተቋማዊ ለውጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሙሉጌታ ቡርቃ በበኩላቸው ዕቅድ አዘገጃጀቱ በተሻሻለ መንገድ የቀረበ መሆኑን ገልጸው የትኩረት መስኮችን በመለየት፣ ዕይታዎችንና ግቦችን በማቀናጀትና ውጤታማ የሆነ ዕቅድ በማቀድ በመጨረሻም አፈጻጸሙን በሚገባ የሚያሳይ ሪፖርት አዘጋጅቶ ማቅረብ በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅ ግንባር ቀደም ተግባር ነው ብለዋል። አክለውም ከዚህ ጋር ተያይዞ ጥራቱንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ መረጃ ፍሰት በየተቋሙ እንዲኖር ሁላችንም የበኩላችንን መወጣት ይገባናል ሲሉ አጠቃለዋል።

ስልጠናውን የተሳተፉ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ ዳይሬክተሮች፣ የቡድን መሪዎች እና የት/ክፍል ሀላፊዎች በየሥራ ክፍላቸው በተለያየ ቡድን በመከፋፈል የጠለቀ ውይይት ያካሄዱ ሲሆን በግብረ መልሱ ጽብረቃ ሰፊ ግንዛቤ ያሳደረ ስልጠና መሆኑን ገልጸዋል። ስልጠናውን በመለጠቅ የኢንስቲትዩቱ የፕላንና መረጃ ማኔጅመንት አስተባባሪ የሆኑት አቶ አስራት ማሙዬ የኢንስቲትዩቱን የ10 ዓመት ስትራቴጂክ መሪ ዕቅድ ያቀረቡ ሲሆን አስቀድሞ በተፈጠረው ግንዛቤ መነሻ የተሳካ ውይይት ተደርጎ ዶ/ር ፋሲካ ሲያጠቃልሉ ይህ በቀጣይነት እስከታችኛው ክፍል ወርዶ የተጧጧፈ ውይይት መካሄድ እንዳለበት በአጽንዖት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በማጠናቀቂያውም ላይ መድረኩን ያዘጋጀው የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ቡድን መድረኩ የታለመለትን ዓላማ ግብ መምታቱን ገልጸው ተሳታፊዎችንና ሌሎች ለዝግጅቱ አስተዋፅዖ ያደረጉትን አባላት በማመስገን ተሰብሳቢዎችን ሸኝተዋል።





# የተለያዩ ኮሌጆች ዓመታዊ የምርምር ግምገማ አካሄደ

ቅንብሩ በሕግኮዳ

## የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት





የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የምርምሮች ግምገማ አውደ ጥናት ባካሄደበት ወቅት የኢንስቲትዩቱ ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ዶ/ር ፋሲካ ቤቴ በመክፈቻ ንግግራቸው ዩኒቨርሲቲው የምርምር ዩንቨርሲቲ እንደ መሆኑ መጠን በምርምር፣ በማህበረሰብ አግልግሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ በጉልህ መሳተፍ እንዳለበት ገልጸው እስካሁን ባለው ሂደት ግን በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚጠበቅበት አንፃር በቂ የሚባል ስራ አለመሰራቱን ጠቁመው ይህንንም ችግር መቅረፍ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

አክለውም በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት (2020/21) የተደረጉ የምርምር ስራዎችን ሲዘረዝሩም 6 የቴማቲክ (Thematic)፣23 የዲሲፕሊኔሪ (Disciplinary) እና አስር ሌሎች ፕሮፖዛሎች መዘጋጀታቸውንና ለዩኒቨርሲቲው መቅረባቸውን እንዲሁም ሴት ተመራማሪዎች 7 ፕሮጀክቶችን ለዩኒቨርሲቲው አቅርበው የገንዘብ እርዳታ በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን አንስተዋል፡፡ በአጠቃላይ በምርምር ስራዎች እና በሌሎች ፕሮጀክቶች ላይ ተሳታፊ የሆኑ ከ70 በላይ አባላት እንዳሉ እና በዚህ አመት ለዚሁ ስራ የተመደበው በጀት ወደ 3.1 ሚሊዮን መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በሌላ በኩል ዩኒቨርሲቲው Ethiopian Journal of Engineering and Technology የተሰኘ ጆርናል ለመመስረት በስራ ላይ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

የምርምር እና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ም/ዳይሬክተር ዶ/ር ተስፋዬ ባዩ በበኩላቸው አውደ ጥናቱ እየተካሄደ ያለው ከዚህ በፊት ተጀምረው ባለቁና በሂደት ላይ ባሉ ችግር ፈቺ ምርምሮች ዙሪያ መሆኑን ጠቅሰው 71 የሚሆኑ ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣ ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እና የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አመራሮች፣ የዲፓርትመንት እና የትምህርት ክፍል ሃላፊዎች እንዲሁም ነባር መምህራንና ተመራማሪዎች ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን ከዚህ የሚገኘው እውቀት የምርምር ስራዎችን ደረጃ ለማሳደግ አይነተኛ ሚና እንደሚኖረው ጠቅሰዋል፡፡

## የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ 4ኛውን ዓመታዊውን የምርምር ግምገማ ባካሄደበት ወቅት የኮሌጁ ዲን ዶ/ር ዳኜ ሽብሩ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ትምህርት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታየውን ድህነት በመቀነስ እና እድገትን በማምጣት ረገድ አይነተኛ ሚና ስለሚጫወት መንግስት ለዚህ ዘርፍ ልዩ ትኩረት መስጠቱን አንስተው በዚህም ረገድ የሚጠበቅበትን ድርሻ ለመወጣት ሶስት ኢንስቲትዩቶች፣ ስምንት ኮሌጆችና ከመቶ የሚበልጡ ዲፓርትመንቶች ያሉት ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በቁርጠኝነት እየሰራ እንዳለ ተናግረዋል፡፡ ኮሌጁ በሥሩ ከአራት ሺህ በላይ በቀን፣ በማታ፣ በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናትና በክረምት መርሐ ግብር የሚማሩ ተማሪዎች፤ ከሁለት መቶ በላይ የአካዳሚክ እንዲሁም ከሀያ አምስት በላይ የአስተዳደር ሰራተኞች ያሉት ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ስምንት የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሰባት የሁለተኛ

ዲግሪ እና ሁለት የፒኤችዲ ፕሮግራሞችን እየሰጠ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

አክለውም ዩኒቨርሲቲዎች ከማስተማሩ በተጨማሪ በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ላይ መሳተፍ ሀላፊነታቸው በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው በዚሁ ዘርፍ ንቁ ተሳትፎ እያደረገ እንደሚገኝ ያብራሩ ሲሆን በዚሁ ግምገማ አስራ አምስት የምርምር ወረቀቶች እንደሚቀርቡ እና ተሳታፊዎች ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ግምገማውን ውጤታማ እንደሚያደርጉት ያላቸውን እምነት ገልጸዋል ፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ የምርምር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ተባባሪ ዲን የሆኑት ዶ/ር መለሰ ማዳ በበኩላቸው የምርምር ስራዎቹ የማህበረሰቡን ችግር ፈቺነታቸው እንደሚገመገም እና የምርምሮቹ ግኝቶች በዩኒቨርሲቲው መጽሔት እና በሶሻል ሚዲያዎች ለኮሌጁ ማህበረሰብ ተደራሽ እንደሚሆን እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃም ለማሳተም ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

## የትምህርት ኮሌጅ

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ኮሌጅ ዓመታዊ የምርምር ግምገማ ባካሄዱበት ወቅት የትምህርት ኮሌጁ ዲን ዶ/ር አብርሃም ቱሉ ኮሌጁ 5 የሶስተኛ፣ 7 የሁለተኛ፣ 13 የመጀመሪያ ድግሪ እና 4 የሰርቲፊኬት ፕሮግራሞችን በመክፈት ከሁለት ሺህ በላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ እያስተማረና ከእነዚህም ውስጥ 320 የድህረ ምረቃ ተማሪዎች መሆናቸውን ገልጸው የኮሌጁ መምህራንም በትምህርት ጥራት ላይ እያጋጠሙ ባሉ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው ላይ ወቅቱን የጠበቀ ችግር ፈቺ ምርምሮችን እየሰሩ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም ከ20 የሚበልጡ ተመራማሪዎች ምርምር እያካሄዱ መሆናቸውን ተናግረዋል፡ ፡ አክለውም ተመራማሪዎችም የሰሯቸውን የምርምር ውጤቶች የተለያዩ ሚዲያዎችንና ማህበራዊ ድረ ገጾችን በመጠቀም ለሳይንሱ ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይም ማሳተም እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ታፈሰ ማቲዎስ ሲናገሩም ለሀገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት ትምህርት ቁልፍ መሳሪያ በመሆኑ ሀገራችንን ማሳደግ ከፈለግን በትምህርትና ትምህርት ጥራት ላይ በርትተን መስራት ይኖርብናል ያሉ ሲሆን የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲም የምርምር ዩኒቨርሲቲ ተብለው ከተለዩት አንዱ እንደመሆኑ ምርምር ላይ ትኩረት ሰጥተን ለመስራት መምህራኖቻችንን በምርምር እንዲሳተፉ ማድረግና አቅማቸውንም ማጎልበት፣ የምርምር ፕሮጀክቶችን መገምገም፣ አዳዲስ የምርምር ጆርናሎችን ማቋቋም፣ የምርምር ውጤቶች በዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ እንዲወጡ ማድረግና የምርምር ፕሮጀክቶችንም ከድህረ ምረቃ ተማሪዎች ጋር ማስተሳሰር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡



# የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ የዓለም የሴቶች ቀንን አከበረ

በተስፋዬ ተ/ማርያም (ኤዲትንግ በሕግኮዳ)

**“የሴቶችን መብት የሚያከብር ማህበረሰብ እንገንባ”** በሚል መሪ ቃል በተከበረው በዚሁ በዓል ላይ የተገኙት የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ኢ/ር ፍሰሀ ጌታቸው በዓለም ለ111ኛ በሀገራችን ደግሞ ለ45 ጊዜ ለሚከበረው የአለም የሴቶች ቀን (March 8) እንኳን አደረሳችሁ በማለት ንግግራቸውን የጀመሩ ሲሆን ከሀገራችንን ሕዝቦች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ቢሆኑም በቁጥራቸውና በሚገባቸው ልክ በሀገሪቱ ላይ ያላቸው ተሳትፎ እምብዛም መሆኑን አንስተው ነገር ግን ይህ አካሄድ የማያዋጣ በመሆኑ እንደ ሀገር ሴቶችን ወደ ፊት ለማምጣት መንግስት በትኩረት እየሰራ ሲሆን ዩኒቨርሲቲውም በበኩሉ የሴት መምህራንን ቁጥር ለማሳደግ በመጀመሪያ ድግሪ የሚመረቁና ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎችን ለመቅጠር መወሰኑን አንስተዋል። ሴቶች ብልህና ለሀቅ የሚወግኑ በመሆናቸው የስልጣን ቦታዎችን ቢይዙ አሁን በዓለማችን ላይ የበዛው ጦርነት፣ መፈናቀልና ሙስና በእጅጉ ይቀንሳል ብለው እንደሚያስቡ ያላቸውንም እምነት ገልጸዋል ።

የዩኒቨርሲቲው የሴቶች ህፃናት ወጣቶችና ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ምህረት ገነነ በዓሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በአሜሪካን ሀገር ከዛሬ መቶ አስራ አንድ አመት በፊት እ.ኤ.አ በ1909 የተከበረ ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተደረጉ ሰፋፊ ትግሎች በአለምአቀፍ እንዲሁም በሀገራችን ደረጃ በረካታ ለውጦች መመዝገባቸውን እንስተው ነገር ግን ገና ብዙ ሊሰራ እንደሚገባ ሀሳባቸውን ገልጸዋል። ሴቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በፖለቲካው ዘርፍ እንደ ወንዶች ሁሉ ንቁ ተሳትፎ ሊያደርጉ እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ያለ ሴቶች የነቃ ተሳትፎ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል ተገንዝበው ሙሉ ድጋፋቸውን ሊያሳዩ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በመጨረሻም ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ሴት ተማሪዎች ሽልማት የተበረከተ ሲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ሴት መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞችም እውቅና ተሰጥቷል። ሽልማቱን ያበረከቱት የዩኒቨርሲቲው አስተዳደርና ተማሪዎች አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሳይ ሀይሉ በግቢው ውስጥ የሚስተዋሉትን የትኛውንም ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችና ጫናዎች ለማስቀረት በከፍተኛ ትኩረት እየተሰራና ውጤትም እየተመዘገበ እንደሚገኝ ገልጸዋል።



# የወንዶ ገነት ደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ እና ጂኦ ፋሻል ኢንፎርሜሽን ሴንተር በተለያዩ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ዙሪያ በጋራ ለመስራት ተስማሙ

በኤፍሬም ዱባለ




ስምምነቱ የተቋማቱን የረጅም ጊዜ ትብብር ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚያሳድገው የተገለጸ ሲሆን የወንዶ ገነት ደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ ዲን ዶ/ር ሞቱማ ቶለራ በስምምነቱ ወቅት እንደገለጹት ኮሌጁ ከ40 ዓመታት በላይ የማስተማር ልምድ ያለው ሆኖ በአከባቢ ጥበቃ፣ በአየር ንብረት ለውጥና በአሬንጓዴ ልማት ስራዎች በርካታ ባለሙያዎችን በማሰልጠንና ወደ ስራ በማሰማራት ሀገራዊ ግዴታዉን እየተወጣ ያለ ተቋም መሆኑን አስረድተዋል፡፡ አያይዘውም ኮሌጁ በአሁኑ ሠዓት በ12 የትምህርት ክፍሎች ከመጀመሪያ እስከ PHD በሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን እያስተማረ መሆኑንም በመግለፅ በቅርቡም የሣይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚንስቴር ባወጣዉ ድልድል መሠረት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በሣይንስና ምርምር ማዕከልነት ከተደለደሉ አንጋፋ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ በመሆኑ ኮሌጁም ይህን መሠረት ባደረገ መልኩ ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በትብብር እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እንደ ዶ/ር ሞቱማ ቶለራ ገለፃ ኮሌጁ በአሁኑ ሰዓት በደንና አከባቢ ጥበቃ (Agroforestry)፣ አሬንጓዴ ልማትና ዘመናዊ የመሬትና ካርታ ስራና ንባብ (GIS) ዘርፎች በትኩረት እየሰራ ሲሆን ዉጤታማ ስራዎች እንዲሰሩ ጆኦ ፋሻል ኢንፎርሜሽን ሴንተር ከዚህ ቀደምም በተግባር ስልጠና፣ በልምድ ልዉዉጥ፣ በገንዘብና ቁሳቁስ በርካታ ድጋፎችን ማድረጉም ተመላክቷል፡፡ የጂኦ ፋሻል ኢንፎርሜሽን ሴንተርን ወክለዉ በስምምነቱ ላይ የተገኙት ዶ/ር ቱሉ ባሻም በበኩላቸዉ እንደገለፁት ተቋሙ ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ወንዶ ገነት ደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ ጋር ለረጅም ጊዜያት በትብብር ሲሰራ መቆየቱን በመጠቆም ይህም ስምምነት የተቋማቱን ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚያሸጋግርም ገልፀዋል፡፡

ስምምነቱን ከዚህ ቀደም ከኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ኢንስትትዩትና ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ጋር መፈራረማቸዉንም ዶ/ር ቱሉ የገለፁ ሲሆን ከአንጋፋዉ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ወንዶ ገነት የደንና ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ ጋር ሶስተኛዉን ስምምነት በመፈራረማቸዉ ደስተኛ መሆናቸዉንም አስታዉቀዋል፡፡ ዘርፉን በምርምርና ቴክኖሎጂ ከማዘመንም ባሻገር በሰዉ ሃይል ስልጠና ፈጣንና ቀልጣፋ የመረጃ ልዉዉጥ ስራዎችም በትብብር ለመስራት ተስማምተዋል፡፡



# በምር/ቴክ/ሽግ/ም/ፕ/ጽ/ቤት የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በሲዳማ ክልል ወንዶገነት ወረዳ ለሚገኙ አርሶ አደሮች ምርጥ ዘሮችን አበረከተ

በስለሺ ነጋሽ



የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬ/ጽ/ቤት በማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት አማካኝነት በተመረጡ ወረዳዎች የተለያዩ የሰብል እና እንስሳት ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅና ተጠቃሚ የማድረግ ስራዎች እየሰራ ሲሆን በሲዳማ ክልል ወንዶ ገነት ወረዳ ለሚገኙ አርሶ አደሮች የእርሻ ምርትና ምርታማነት እንዳይቀንስ መንግስት እየሠራ ያለውን ሥራ ለመደገፍና አዲስ ዝርያዎችን ለማላመድ የተሻሻለ የፕሮቲን በቆሎ ዝርያ አበረከተ፡፡

የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የነበሩ ዶ/ር ፍሬው ካሱ ይህ የበቆሎ ዝርያ ፖይነር በመባል የሚታወቅ ሲሆን ከሌሎች የበቆሎ ዝርያዎችም የሚለየው የፕሮቲን ይዘት ያለው በመሆኑ ተመጋቢዎች ከእንስሳት ተዋጾዎች የሚያገኙትን ፕሮቲን በዚህ የበቆሎ ዝርያ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል ብለዋል፡፡ አክለውም ይሄንን የበቆሎ ዝርያ ከወረዳው እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት ጋር በመሆን በወተራና ቀጨማ፣ አሩማ እና ዩዎ ሶስት ቀበሌዎች ለሚገኙ 32 አርሶ አደሮች መከፋፈሉንና ከዚህ በፊትም በተያዘው ዓመት በመኸር የሚዘራ 10 ኩንታል ሹሩሜ በመባል የሚታወቅ ስንዴ ዝርያ እና ኢቦኒ የሚባል የገብስ ዝርያ እንዲሁም የተሻሻለ የቦንጋ የበግ ዝርያ ለአርሶ አደሮች መከፋፈሉን ገልጸው አርሶ አደሮችም የተሰጣቸውን የበቆሎ ዝርያ በአግባቡ በመዝራት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዳለባቸውና ሌሎች አርሶ አደሮችም ይሄንን ልምድ በመቅሰም የማስፋትና የማላመድ ስራዎችን መስራት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡



# በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በእምቦጭ መጤ አረምና ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ የምክክር አውደ ጥናት ተካሄደ

በተስፋዬ ተ/ማሪያም (ኤዲትንግ በሕግኮዳ)

የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ጥናት ማዕከል ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬ/ጽ/ቤት ጋር በመተባበር የምክክር አውደ ጥናት ባካሄደበት ወቅት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የምር/ቴክ/ሽግ/ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ታፈሰ ማቴዎስ የእምቦጭ አረም በ1950ዎቹ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባና መጀመሪያ አባ ሳሙኤል በሚባለው የውሀ ማጠራቀሚያ እንደታየ ገልጸው አረሙ ወደ ቆቃ ሀይቅ እንደተዛመተ እንዲሁም ጥንቃቄ ባለመደረጉ በአሁኑ ሰዓት የዝዋይና አባያ ሀይቆችን ወሮ እንደሚገኝ አብራርተዋል:: እንደ ሀዋሳ ሀይቅ ያሉ የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች በአረሙ የመወረር ከፍተኛ ስጋት እንዳለባቸው ጠቁመው ይህ ከመከሰቱና ጉዳቱ መመለስ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት ፈጣንና የተቀናጀ የቁጥጥር ስራ መሰራት እንዳለበት አሳስበዋል::

የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ጥናት ማዕከል ዋና ኃላፊ ዶ/ር ጌታቸው ስሜ  ስለምክክር አውደ ጥናቱ ዓላማ ሲያስረዱ በ8 በስምጥ ሸለቆ ዙሪያ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል እውቀትንና ልምድን ለመለዋወጥ መታሰቡን ገልጸው አካባቢው የበርካታ ዉሀ ሀብቶች ባለቤት የሆነና ለአካባቢው ህብረተሰብ ህይወት መሰረት የሆነ ቢሆንም እኚህ የውሀ አካላት ባልተገባ የሰው ልጅ ድርጊቶች ጉዳት እየደረሰባቸው ይገኛል ብለዋል:: በዋናነትም የወንዞችና ሀይቆች በዚህ መጤ አረም መወረር በስነ-ምህዳሩና የሰዎች ህይወት ላይ ከፍተኛ አደጋ መደቀኑን አንስተዋል::

በመጨረሻም በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ መምህር እና ተመራማሪ የሆኑት ዶ/ር ግርማ ጥላሁን የሀዋሳ ሀይቅ በአካባቢው እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ በርካታ ጎብኚዎች ያሉትና በዙሪያው ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የገቢ ምንጭ የሆነ ሳቢ ሀይቅ መሆኑን ገልጸው ነገር ግን ሀይቁ እየሰጠ ባለው አግልግሎት ልክ በቂ ጥበቃ እየተደረገለት ባለመሆኑ ሌሎችም የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች በመጤ እምቦጭ አረም የተጋረጠባቸውን አደጋ በመለየት በመፍትሄ አቅጣጫዎች ላይ የጋራ ስምምነት ላይ ለመድረስ እንደሚገባ ገልፀዋል::





# የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የማህበርሰብ አግልግሎት ዳይሬክቶሬት የአካባቢውን ማህበረሰብ ትኩረት ያደረጉ በርካታ ተግባራትን አከናወነ

በሕግኮዳ የተቀነባበረ



## በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ ስር ለሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ሳይንስ መምህራን የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጠ

የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የነበሩት ዶ/ር ፍሬው ካሳ ለሲዳማ ክልል እና ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር በተለያዩ ወቅቶች በግብርና፣ አካባቢ ጥበቃ፣ ጤና እና ምግብ አጠባበቅ እንዲሁም የትምህርት ዘርፎች በርካታ ስልጠናዎችን እየተሰጠ እንደሚገኝ ገልጸው በከተማ አስተዳደሩ ስር ከሚገኙ 13 የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ 26 የሳይንስ መምህራን ተሳታፊ መሆናቸውን ጠቁመዋል:: ስልጠናው በዋናነት የሚያተኩረው በባዮሎጂ እና ኬሚስትሪ የትምህርት ዘርፎች ላይ መሆኑንና ለእነዚህ የትምህርት ዘርፎች አስፈላጊ በሆነው የላብራቶሪ አጠቃቀም ላይ ሰልጣኞች የተሻለ እውቀት እንዲኖራቸውና ይህን ያገኙትን እውቀት ለሌሎች መምህራን እና ለተማሪዎቻቸው እንዲያጋሩ በማድረግ ላይ መሆኑን ገልጸዋል:: ዩኒቨርሲቲው ከስልጠናው በተጨማሪም አስፈላጊ የሆኑ የላብራቶሪ ቁሳቁሶችን ድጋፍ እንደሚያደርግም ቃል መግባቱን ተናግረዋል::

በማህበረሰብ አግልግሎት ዳይሬክቶሬት የትምህርት እና ስልጠና ባለሙያ አቶ ጌታቸው ያዬ በበኩላቸው ስልጠናው የመጀመሪያ ዙር መሆኑን እና በዚህ የሚያበቃ እንዳልሆነ በመግለጽ በቀጣይ በሌሎች የትምህርት መስኮችም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል::

በመጨረሻም በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የትምህርት መምሪያ የትምህርት አመራር ልማት ስራ ሂደት ባለሙያ የሆኑት አቶ ገዛኸኝ ደገፉ የማህበረሰብ አገልግሎት ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ስልጠና እና ድጋፍ ሲያደርግ የነበረ መሆኑን አስታውሰው ምስጋናቸውን አቅርበው ይህ ትብብር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያላቸውን እምነት ገልጸዋል::

## በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ ስር ለሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ርዕሰ መምህራን ስልጠና ተሰጠ

የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት ዩኒቨርሲቲው ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ስር ከሚገኙ 14 የመንግስት ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ 42 አስተዳደር አካላት እየተሰጠ ያለ ስልጠና መሆኑን ተናግረው በቀጣይ የሚሰጡ ስልጠናዎች ሌሎች በቅርቡ በተደረገው ጥናት የተለዩ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን አካቶ በዚያው መሰረት የሚካሄድ መሆኑን ጠቁመው በተጨማሪም የማቴራይል ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸውም በሚያቀርቡት ፕሮፖዛል መሰረት እርዳታው የቀጥላል ብለዋል::

የዘርፉ ባለሙያ አቶ ጌታቸው ያዬ በበኩላቸው ትምህርት የሁሉም ነገር መሠረት መሆኑን ጠቅሰው ርዕሰ መምህራኑ ከዚህ ስልጠና በሚያገኙት እውቀት ራሳቸውን ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር በማራመድ በመማር ማስተማሩ፣ በአመራር ብቃትና በትምህርት ጥራት ዙሪያ የሚታየውን ችግር ለመቅረፍ አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ የሚል እምነት አለኝ ብለዋል::





## ከሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ጋር በመተባበር ኑሯቸውን በጎዳና ላይ ላደረጉ የማህበረሰብ ክፍሎች ስልጠና ተሰጠ

ዳይሬክተሩ በንግግራቸው ዩኒቨርሲቲው ለሀዋሳ ከተማ አስተዳደር በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ ዘርፎች በርካታ ስልጠናዎችን የሰጠ እና የማቴራያል ድጋፍ ያደረገ መሆኑን ጠቁመው የአሁኑ ስልጠና በከተማ አስተዳደሩ ስር ከሚገኙ ከሐይቅ ዳር፣ ባህል አደራሽ፣ መሀል እና ምስራቅ ክፍለ ከተሞች ለተውጣጡ 50 ጎዳና ተዳዳሪዎች የተሰጠ የአቅም ግምባታ ስልጠና መሆኑን ገልጸዋል:: ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በተገባው ውል መሰረትም ለ250 ጎዳና ተወዳዳሪዎች እና ስራ አጥ ወጣቶች በሶስት ዘርፎች ማለትም በዶሮ እርባታ፣ በከተማ ውበት እና በጫማ መጥረግ/ሊስትሮ ስራ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እና የማቴራያል ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስረድተዋል::

አቶ ጌታቸው ያዬ በበኩላቸው እነዚህ በጎዳና ላይ ህይወታቸውን እየመሩ ያሉ ልጆች የማህበረሰቡ አንድ አካል ስለሆኑ ሳይንሳዊ የሆነ ስልጠና እና ድጋፍ ካገኙ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር ነገያቸውን የማየት ሕልም ይኖራቸዋል ብለዋል::

የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የእንስሳት እርባታ እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ባለሙያ የሆኑት አቶ ጋሻው ቢኖ ቀደም ሲል በሲዳማ ክልል በለኩ እና ሀዋሳ ከተማ በሚገኙት ዳቶ እና ጨፌ ኮቲ ጀቤሳ በዶሮ እርባታ ዘርፍ ለሰለጠኑ ስራ አጥ ወጣቶች ጫጩት እና መኖን ጨምሮ ለእያንዳንዱ ሰልጣኝ የ1500 ብር ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደስራ መግባታቸውን ገልፀው ስልጠናው ላይ ለሚገኙ እና በጫማ መጥረግ/ሊስትሮ ስራ ላይ ለሚሰማሩ የሊስትሮ ሼዶች በጨረታ ሂደት ላይ እንዳሉ አንስተው የከተማውን ውበት በጠበቀ መልኩ ተመቻችተው ለሰልጣኞች እንደሚቀርቡ ተናግረዋል::



# የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ መራሒት ክበብ በሴት ተማሪዎች ዙሪያ ልዩ ፕሮግራም አዘጋጀ

በሕግኮዳ

የመራሒት ክበብ አባላት “**እንዲትም ሴት በወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ ማጣት ምክንያት ከትምህርት ቤት መቅረት የለባትም**” በሚል መሪ ቃል ልዩ ልዩ ዝግጅቶች፣ ኤግዚቢሽን እና የሞዴስ ማሰባሰብ ስራ ተግባር ፈጽሟል፡፡

ተማሪ ተቋም አማረ “መራሒት” የሚለው የክበቡ ስያሜ የጣሊያን ቃል መሆኑንና ትርጓሜውም **መሪ ሴት** መፍጠር መሆኑን ገልጻለች፡፡ ክበቡ ቀደም ሲል የልጃገረዶች ክበብ ቢባልም ነገር ግን የወር አበባ ጉዳይ የሁሉም ሴት ጉዳይ በመሆኑ ስያሜውን መለወጥ ማስፈለጉን አስረድታለች፡፡ ክበቡ በተለያዩ ቡድኖች ተከፋፍሎ በወንዶ ገነት፣ አዋዳ እና ዋናው ግቢ የንጽህና መጠበቂያ እጥረት ለሚያጋጥማቸው ተማሪዎች ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ የክበቡ ዓላማ ለሴቶች እና ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ የወር አበባ የተፈጥሮ ግዴታ መሆኑንና የንፅህና መጠበቂያ አስፈላጊነት ላይ ግንዛቤ መፍጠር መሆኑን ተናግራለች፡፡ ይህ ዝግጅት በዚህ ደረጃ በዩኒቨርሲቲ ሲከበር ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑን እና በዚህም ምክንያት ለዩኒቨርሲቲው ምስጋና ማቅረብ እንደምትፈልግ ገልጻለች፡፡

ተማሪ ቤተል ጥበቡ በበኩሏ ሴቶች የወር አበባቸው ሲመጣ የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ተለምዷዊ ቁሳቁሶች በጤንነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚኖረው በመግለጽ ክበቡ ተለምዷዊውን በማስቀረትና ተገቢውን የንጽህና መጠበቂያ ከመጠቀም አንጻር ግንዛቤ በመፍጠር ብሎም በማቅረብ የሴቶችን የአካልና አዕምሯዊ ስብራት ለመጠገን እየሰራ እንደሚገኝና የሚመለከተው ሁሉ ቀና ትብብር እንዲያደርግ ጥሪዋን አቅርባለች፡፡

በመጨረሻም የክበቡ አባላት ቤተሰብ ለቀለብ ከሚልክላቸው ቀንሰው በማሰባሰብ የገዟቸውን የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ፣ ሳሙና እና የውስጥ ልብሶች ለዩኒቨርሲቲው የሴቶች ህፃናትና ኤች.አይ.ቪ. ዳይሬክቶሬት አስረክበዋል፡፡ የዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር ወ/ሮ ምህረት ገነነ የክበቡ አባላት ደመወዝተኛ የሆኑ ብዙዎች ያላሰቡትን ይህን ሀሳብ በማሰባቸው አኩሪ ስራ መስራታቸውን ገልጸው የሥራ ክፍላቸው ከክበቡ ጋር በቅርበት ለመስራትና አስፈላጊውን ትብብር ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡





# የሳይንስና ቴክኖሎጂ እና ምንድስና ማዕከል በሮቦቲክስ ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች አስመረቀ

በተስፋዬ ተ/ማርያም (ኤዲትንግ በሕግኮዳ)






በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲው የሳይንስ ማዕከል በተካሄደው የምረቃ ሥነ-ስርዓት ስልጠናውን የወሰዱ 24 ተማሪዎች የተመረቁ ሲሆን ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ 7 ተማሪዎች ሽልማት ተበርክቶላቸዋል::

የማዕከሉ ኃላፊ ዶ/ር ምስራቅ ጌታሁን እንደገለጹት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምህንድስና ማዕከል (STEM center) በሚስተር ገልፋንድ ድጋፍና መስራችነት በ2007 ዓ.ም እንደተመሰረተና ስራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በሳይንስ፣ ሂሳብ፣ ሮቦቲክስና ኤሌክትሮኒክስ የትምህርት ዘርፎች የአንደኛ መለስተኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን እና መምህራንን በማሰልጠን ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል:: ማዕከሉ በአሁኑ ወቅት 12 ከ7ኛና 8ኛ ክፍል እንዲሁም 60 ከ9ኛና 10ኛ ክፍል የተውጣጡ ተማሪዎችን ተቀብሎ እያስተማረ እንደሚገኝ አስታውቀዋል::

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የፕሮጀክቶች ትስስር ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እና በዕለቱ የምር/ቴክ/ሽግ/ም/ፕሬዝዳንት ተወካይ ዶ/ር መብራቱ ሙላቱ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው በዚህ ዘርፍ ትኩረት በመስጠት የSTEM ማዕከሉን በተለያዩ መስኮች በማገዝ ብቁና ፈጣሪ ታዳጊዎችን ለመፍጠር እየሰራ እንደሚገኝ አስረድተዋል::

የSTEM power የሀገር ውስጥና የምስራቅ አፍሪካ ተጠሪ እና የዕለቱ የክብር እንግዳ የሆኑት ወ/ሪት ቅድስት ገብረ አምላክ ማዕከሉ ከተመሰረተ 11 አመት ማስቆጠሩን ጠቅሰው 48 ከሚጠጉት ማዕከላት መካከልም በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው ማዕከል እጅግ ውጤታማ ከሆኑት ማዕከላት አንዱ መሆኑን ገልጸው ከምረቃው ባሻገር ከዩኒቨርሲቲው ጋር በበለጠ በጋራ ለመስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ሰነድ ለመፈራረም መገኘታቸውን ተናግረዋል::

በመጨረሻም የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር አያኖ በራሶ ማዕከሉ መጀመሪያ በተቋቋመበት ወቅት በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ዘንድ ሙሉ ግንዛቤ ያልነበረ መሆኑን አውስተው፤ በአሁኑ ወቅት ግን ዘርፉ የመንግስት ትኩረት እየሆነ የመጣ መሆኑንና ዩኒቨርሲቲውም ከፍተኛ ትኩረት እንደሰጠው አስረድተው የመግባቢያ ስምምነቱም ዩኒቨርሲቲው ከማዕከሉ ጋር የበለጠ እንዲሰራና ውጤታማ እንዲሆን እንደሚያደርገው ያላቸውን እምነት ገልጸዋል::



# የስነምግባርና ጸረ-ሙስና መከታተያ ዳይሬክቶሬት የተማሪዎች ጥያቄና መልስ ውድድር አካሄደ

በስለሺ ነጋሽ



በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና መከታተያ ዳይሬክቶሬት የፌደራል የስነ-ምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን የተመሰረተበትን 20ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ለተማሪዎች የጥያቄና መልስ ውድድር አዘጋጅቷል፡፡ ከሰባቱም ካምፓሶች የጥያቄና መልስ ውድድር በማድረግ አብላጫ ውጤት ላመጡት ተወዳዳሪ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ደረጃ የአሸናፊዎች አሸናፊ የተለየ ሲሆን ለአሸናፊዎቹም ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አየለ አዳቶ በዕለቱ ተገኝተው በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን የስነምግባር ጥያቄ አንገብጋቢ፣ አሳሳቢ፣ በጣም አስፈላጊና ቀጣዩስ ትውልድ ምን ይጠብቀዋል በምንልበት ወቅት የስነ ምግባር ጉዳይ ይመለከተኛል ብላችሁ ይህን ፕሮግራም ያዘጋጃችሁና የተገኛችሁ በተለይ ደግሞ የዕለቱ ተወዳዳሪ ተማሪዎች ታላቅ ምስጋና ይገባችኃል ብለዋል፡፡ አክለውም እንደተናገሩት የዛሬው ተወዳዳሪዎችም ስነምግባራቸውን በማስቀጠል በአሸናፊነት እና በእችላለሁ መንፈስ በዩኒቨርሲቲያችን ብቻ ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃም አሸናፊ በመሆን የሚያጋጥሟችሁን በርካታ ሰንካላ አስተሳሰቦች እና አመለካከቶችን በመቋቋምና በመወጣት ፍቅርን፣ ሰላምን እና አንድነትን በመስበክ የበኩላችሁን እንድትወጡ አደራ እላለሁ ብለዋል፡፡

የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና መከታተያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ከበደ ኩማ እንደገለጹት ተማሪዎች ከብሄርተኝነትና ከኃይማኖት ጽንፈኝነት የጸዳ አስተሳሰብ በመያዝ፣እርስ በእርስ ሰላማዊ ግንኙነት በመፍጠር፣ በመቻቻል መንፈስና የተቋሙን ህግና ደንብ በማክበር ለሰላም ተቆርቋሪ መሆን ይኖርባችኃል ብለዋል፡፡

በዕለቱም ከሴቶች ተማሪ አምላክ ስዩም ከዋናው ግቢ እንዲሁም ተማሪ ባህሩ ዘውዴ ከወንዶ ገነት ኮሌጅ አሸናፊ በመሆን የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲን የሚወክሉ መሆኑ ተገልጾ ለተወዳዳሪዎችም የምስክር ወረቀት በመስጠት ፕሮግራሙ ተጠናቋል፡፡



# ግብርና ኮሌጅ በከብቶች ላይ እየሠራ በሚገኘው ምርምር ዙሪያ ገለጻ ከማድረጉ ባሻገር የመስክ ጉብኝት አካሄደ

በተስፋዬ ተ/ማርያም (ኤዲትንግ በሕግኮዳ)

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ኮሌጅ የእንስሳት አያያዝና የከብት ግጦሽ ተመራማሪዎች በዋናው ግቢ በምርምራቸው ዙሪያ ገለጻ አድርገዋል:: በገለጻው ላይ ከደብብ እና ሲዳማ ክልሎች እንዲሁም ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት ባለድርሻ አካላት የተጋበዙ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር አያኖ ባራሶ ዩኒቨርሲቲው ከዓለም አቀፍ አጋሮቹ ጋር በመሆን ከ62 በላይ የሆኑ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶችን ቀርጾ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸው የLivestock system innovation Lab (LSIL) በዩኒቨርሲቲው እየተካሄዱ ካሉ ፕሮጀክቶች አንዱ መሆኑንና ዋነኛ ትኩረቱንም በእንስሳት መኖና ስነ-ምግብ፣ በወተት እና የወተት ከብቶች አያያዝ፣ የከብቶች ስጋና ስነ-ምግብ እንዲሁም የምግብ ደህንነት ላይ ያደረገ መሆኑን ተናግረዋል:: ፕሮጀክቱ እ.ኤ.አ በ2017 በበርካታ ተቋማት የጋራ ትብብር ተቀርጾ የተጀመረና አሜሪካን ሀገር በሚገኘው University of Florida የሚተዳደር ሲሆን በአሁኑ ወቅት ወደ መጠናቀቁ የደረሰ ፕሮጀክት ነው ብለው ለፕሮጀክቱ መሳካት ከዩኒቨርሲቲው ጋር በትብብር ለሰሩ ተቋማት እና ግለሰቦች ምስጋናን አቅርበዋል::

የእንስሳት ሳይንስ ትምህርት ክፍል ሀላፊና ተመራማሪ ዶ/ር ስንታየው ይግረም በበኩላቸው አገራችን ኢትዮጵያ በቀንድ ከብት ሀብቷ የታወቀች ብትሆንም በእንስሳት አያያዝና የመኖ አቅርቦት ዙሪያ በሚስተዋሉ ችግሮች የተነሳ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም ሳታገኝ ብትቆይም ችግሩን ለመቅረፍ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች በLSIL ፕሮጀክት ባገኙት ድጋፍ ታግዘው ችግር ፈቺ ምርምር ሲያካሂዱ የቆዩ ሲሆን ስለደረሱበት ውጤት ለባለድርሻ አካላት ገለጻ የሚያደርጉና የመስክ ጉብኝት የሚያካሂዱ ይሆናል ብለዋል:: እንዲሁም ዩኒቨርሲቲው በዘርፉ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ተመራማሪዎች የሚያገኟቸውን አዳዲስ ግኝቶች ከአምራቹ ማህበረሰብ ጋር ለማገናኘት እንዲያስችለው በዘርፉ የተማሩ ባለሙያዎችን ቁጥር ለማሳደግ 7 ተጨማሪ የፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል::




የLSIL ፕሮጀክት አስተባባሪና ተመራማሪ ፕ/ር አዱኛ ቶሌራ ከመስክ ጉብኝቱ በኋላ በሰጡት መግለጫ ምርምሩ የተጀመረው በውጭ ሀገር ዲቃላ ከብት ላይ ቢሆንም ለወደፊት በሀገር በቀል ከብቶች ላይ እንደሚቀጥል ተናግረው የእንስሳት ወተት የህፃናት መቀንጨር ችግርን ለመፍታትና የአዕምሮ እድገታቸውና የማሰብ ችሎታቸው ለማሳደግ አይነተኛ ሚና እንዳለው ጠቁመው በእንስሳት መኖ አቅርቦት ማነስ ምክንያት በዘርፉ ላይ የሚታዩ ማነቆዎችን ለመቀነስ የመንግስት የፖሊሲ ለውጥ፣ የባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎና በሙያው የሰለጠኑ ምሁራን በእንስሳት ጤና ላይ የየበኩላቸውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል ብለዋል::

በመጨረሻም የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የምር/ቴክ/ሽግ/ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ታፈሰ ማቴዎስ ከተሳታፊዎች ለተነሱ ጥያቄዎች በተመራማሪዎቹ መልስና ማብራሪያ እንዲሰጥ ከመምራታቸው ባሻገር በእንስሳት ተዋፅኦ ምርት መቀነስና የመኖ እጥረት ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችን ለማሻሻል በዚህ ገለጻና ውይይት ላይ የተነሱ መፍትሄዎች አይነተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል::

# የ6ኛው ሀገራዊ ብሔራዊ ምርጫ ሂደት ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ምቹ አውድ ከመፍጠር አንፃር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚና የላቀ መሆኑ ተገለጸ

በተስፋዬ ተ/ማ (ኤዲትንግ በሕግኮዳ)








በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የምር/ቴክ/ሽግ/ም/ፕ/ጽ/ቤት እና የሕግና ገቨርናንስ ኮሌጅ በጋራ በመሆን የፓናል ውይይቱንና የምክክር መድረኩን ያዘጋጁ ሲሆን ውይይቱ በአካል እና በበይነመረብ ተካሂዷል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር አያኖ በራሶ በሀገራችን የምርጫ ስርዓት በህገመንግስት ተደንግጎ ከወጣው ከ1923 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን የምርጫ ሂደት በዳሰሱበት ወቅት በንጉሱ  ዘመነ መንግስት ህዝቡ የራሱን መሪ የማይመርጥበት እና “ስዩመ እግዚአብሔር” የተባለ መለኮታዊ ስርዓትን ይከተሉ የነበረ ሲሆን በደርግ ዘመነ መንግስት ደግሞ የአንድ ፓርቲ ስርዓት የነበረበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡  በኢህአዴግ ዘመነ መንግስት አንፃራዊ መሻሻል የተስተዋለና የመድብለ ፓርቲ ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃ እና ዴሞክራሲያዊነታቸው ላይ ከፍተኛ ችግር ነበረባቸው ብለዋል፡፡ ላለፍሩት በርካታ ዓመታት የተካሄደው ምርጫ በየወቅቱ የነበሩ መንግስታት ለራሳቸው በሚመች አኳኋን ሲያካሂዱት የነበረ ሲሆን በዚህም የተነሳ የዳበረ የዴሞክራሲ ባህል መገንባት አለመቻሉን አውስተው ከፊታችን ያለው 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ብዙ እድሎችንና ፈተናዎች የያዘ እንደመሆኑ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለምርጫው በሰላም መጠናቀቅና በብዙዎች ዘንድ የተሰነቀውን የዴሞክራሲ ተስፋ የሚያመጣ እንዲሆን በትኩረት እንዲሰሩ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የሳይንስ እና የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ሳሙኤል ክፍሌ በቪዲዮ ኮንፈረንስ ባስተላለፉት መልዕክት ቀደም ሲል በሀገሪቱ ይካሄዱ የነበሩ ምርጫዎች ስለነበሩባቸው ክፍተቶች ከገለፁ በኃላ የዘንድሮው ሀገራዊ ምርጫ ከእነዚህ ስህተቶች እርምትን በመውሰድ የዴሞክራሲ ትንሳኤን ያበስር ዘንድ የብዙ ምሁራን መፍለቅያና መገኛ የሆኑት ዩኒቨርሲቲዎች ዓይነተኛ ሚና መወጣት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡

በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የፖለቲካ ጉዳዮች አማካሪ የሆኑት አቶ ፍስሀ ይታገሱ በቪዲዮ ኮንፍረንስ ባስተላለፉት መልዕክት የዘንድሮ ሀገራዊ ምርጫ ስኬታማ ይሆን ዘንድ መንግስት በቁርጠኝነት እየሰራ መሆኑን ገልፀው ምርጫውን ለማስተጓጎል በሀገር ውስጥም ሆነ ከባህር ማዶ ካሉ ሀይሎች የሚሰነዘሩ ተግዳሮቶችን በጋራ ማለፍ እንደሚገባ ጠቅሰው የተፎካካሪ ፓለቲካ ፓርቲዎችም በሀገሪቱ ከዚህ በፊት በስፋት ከተለመደው የሴራ ፖለቲካ ተላቀው በሀሳብ የበላይነት ብቻ አሸናፊ ለመሆን እንዲሰሩ እንዲሁም የፀጥታና የፍትህ ተቋማት በገለልተኝነት ስራቸውን እንዲያከናውኑ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

የፓናል ውይይቱና የምክክር መድረክ ላይ በአካል እና በበይነመረብ በርካታ አካላት ተሳታፊዎች ሲሆኑ የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮችም ተሳትፈው ለባለድርሻ አካላቱ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ በውይይቱም ከፍተሀዊነት፣ ከፀጥታ ጉዳዮች እና ከሴቶች ተሳትፎ አንጻር ለጋራ እንቅስቃሴ ረብ ያላቸው ገንቢ ሀሳቦች የተሰነዘሩ ሲሆን ተሳታፊዎች ሀላፊነት በተሞላበት መንፈስ የድርሻቸውን እንዲወጡና ለሀገራቸው ጉዳይ ማንኛውንም መሥዋዕት እንደሚከፍሉ ቃል ገብተው ኮንፍረንሱ አብቅቷል፡፡

# የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ጋር በመሆን ለሚመለከታቸው ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ስልጠና ሰጠ

በስለሺ ነጋሽ







የምር/ቴክ/ሽግ/ም/ፕ/ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጥቷል፡፡ ስልጠናው በአእምሯዊ ንብረት መብት ደንቦችና መመሪያዎች፣ በመረጃ አፈላለግ፣ በቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ድጋፍ ዙሪያ ሲሆን ከተለያዩ የስራ ክፍሎች የተውጣጡ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

የምር/ቴክ/ሽግ/ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ታፈሰ ማቲዮስ ዩኒቨርሲቲያችን ረጅም የምርምር ታሪክ እና ከተወሰኑ ዓመታት ጀምሮ ደግሞ በቴክኖሎጂና ፈጠራ፣ ሽግግርና ማስፋት ዙሪያ ትኩረት በመስጠት ለተመራማሪዎችና ለተማሪዎች ድጋፍ በማድረግ በርካታ ስራዎች እየሰራ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው የአእምሯዊ ንብረት መብት ደንቦችና መመሪያዎች ባለመኖራቸው ዩኒቨርሲቲውም ሆነ ተመራማሪዎቹ በቂ በሚባል ደረጃ ተደራሽና ተጠቃሚ ባለመሆናቸው ስልጠናው ማስፈለጉን ተናግረው ከዓለም አቀፍና ከኢትዮጵያ የአእምሯዊ ንብረት መብት ደንቦችና መመሪያዎች  በመነሳት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተዘጋጀው ረቂቅ ሰነድ ላይ በመወያየት ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመላከትና በኢንዱስትሪ ትስስርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት የተሰሩና እየተሰሩ ባሉ ስራዎች፣ እያጋጠሙ ባሉ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ ውይይት እንደሚደረግ በመክፈቻው ላይ ገልጸዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ትስስርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር ባዩ ቡንኩራ በበኩላቸው ዳይሬክቶሬቱ የተቋቋመበትን ዓላማ፣ እስካሁን የሰራቸውን እና እየሰራ ያለውን ተግባራት በዝርዝር ያቀረቡ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ሶስት የቴክኖሎጂ ማበልጸጊያዎች በመክፈት ተማሪዎች ሃሳባቸውን ወደ ተግባር ለመለወጥ ልምምድ እንዲያደርጉ ድጋፎችን እያደረገ እንደሆነ እና ተመራማሪዎችም አስፈላጊው ድጋፍ እተደረገላቸው በርካታ ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማድረግ ለህብረተሰቡ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ለሚገኙ የኒቨርሲቲዎች ማስተማሪያ የሚሆን የምህንድስና ሀይድሮሊክ ማሽን በሽያጭ በማስረከቡ እንደሀገርም ከውጭ የሚገቡትን የማስተማሪያ መሳሪያዎች በማስቀረት የውጭ ምንዛሪን ማስቀረቱን ገልጸዋል፡፡



# ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተለያዩ ተግባራትን አከናወነ

በሕግኮዳ ተቀነባበረ





## የልምድ ልውውጥ አውደ ርዕይ ተዘጋጀ

በJhpiego ድጋፍ ለ8 የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በሕክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በተካሄደው አውደ ርዕይ ከየዩኒቨርሲቲዎች ጤና ሳይንስ ኮሌጆች፣ የአጋር ተቋማት ተወካዮች፣ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህራን እና የአስተዳደር ሰራተኞች ተሳታፊ ሆነዋል::

የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ዶ/ር አንተነህ ጋዲሳ ኮሌጁ ምስረታውን ካደረገበት ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ በየጊዜው ደረጃውን በማሳደግ የትምህርት ክፍሎቹን እና የሚቀበላቸውን የተማሪዎችን ቁጥር እየጨመረ መቷል ብለዋል:: ኮሌጁ በአሁኑ ወቅት የስፔሻሊቲ፣ የድህረ ምረቃ እና የፒ.ኤች.ዲ ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን በኮምፕሬንስቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ደረጃ ከ450 በላይ አልጋዎች ያሉት እና 20 ሚሊዮን ለሚጠጉ የማህበረሰብ ክፍሎች በቋሚነት አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ ገልጸው ከመደበኛ ሕክምና ጎን ለጎን በአሁኑ ወቅት የኮቪድ-19 ማዕከል በመሆን እያገለገለ ይገኛል ብለዋል::

የኮሌጁ ትምህርት ጥራት ቁጥጥር እና ማረጋገጫ አስተባባሪ ዶ/ር አለማየሁ ቶማ በበኩላቸው ኮሌጁ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅና ለማሳደግ በብዙ መልኩ የተለያዩ ተግባራትን መከናወኑንና ከእነዚህም መካከል ተመሳሳይነት ያላቸውን የትምህርት ክፍሎች የላብራቶሪ አገልግሎትን በጋራ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የሀብት ብክነትን ለመቀነስ መቻሉን፣የተማሪዎች ፈተና አሰጣጥና ምዘናን በማሳደግ፣ የመማርያ ክፍሎችንና የትምህርት ግቢውን ለተማሪዎች ምቹና ተስማሚ ለማድረግ በርካታ ስራዎች መሰራታቸውንና ለውጤታማነቱም የJjpiego ድጋፍ አይነተኛ እንደነበር አስረድተዋል::

በዝግጅቱ ተሳታፊ ከነበሩት መካከል የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የትምህርት ጥራት እና ማረጋገጫ አስተባባሪው ሬ/ፕ/ር ረታ ፀጋዬ ዩኒቨርሲቲያቸው የአዲሱ ትውልድ ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ መጠን ነባር ከሆኑና በርካታ ልምድ ካላቸው ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የሚደረገው የልምድ ልውውጥ በእጅጉ እንደሚጠቅማቸው ተናግረዋል::

## ለኮሌጁ መምህራኖችና ጤና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጠ

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ለኮሌጁ መምህራኖችና ጤና ባለሙያዎች ለ5ኛ ጊዜ በዲጅታል ዳታ ኮሌክሽን (መረጃ አሰባሰብ)፣ ኳሊቴቲቭ ሪሰርች አሰራር ላይ፣ ግራንት (ድጋፍ ማግኛ) አጻጻፍ ላይ፣ ሲስተማቲክ ሪቪው ፈንድ ሜታ አናሊሲስ ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጥቷል::

የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ረ/ፐ አለሙ ጣሚሶ ኮሌጁ የምርምር ኮሌጅ እንደመሆኑ የኮሌጁ መምህራንና ባለሙያዎች በህክምናው፣ በትምህርት አሰጣጥ እና በማህበረሰብ አገልግሎት ከሚሰጧቸው ግልጋሎቶች በተጨማሪ የምርምር ፕሮጀክት የመጻፍ፣ የማሳደግና ድጋፎችን አፈላልጎ በማግኘት የመስራት ሙያዊ ክህሎት ሊያዳብሩ የሚሰጥ ስልጠና ሲጠናቀቅ የህብረተሰቡን ችግር የሚፈታ ምርምሮችን የሚያደርግ የተማረ የሰው ኃይል እንደሚኖር እና በቁጥርና በጥራት ደረጃ የተሻሉና የተለዩ ችግር ፈቺ ምርምሮችም ይሰራሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል::





## የማህበረሰብ ቀን በዓል በበንሳና ዳዬ ወረዳዎች ተከበረ

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የማህበረሰብ ቀን በዓል ሲከበር ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት የተሰጠ ሲሆን የስኳር፣ የግፊት እና ከመጠን በላይ ውፍረት በሽታን በመመርመር ልየታ ሲደረግ በሲዳማ ክልል በበንሳና ዳዬ ወረዳዎች በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

የኮሌጁ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ረ/ፕ አለሙ ጣሚሶ እንዳሉት በወረዳዎቹ  ከ20 ሺህ በላይ ነዋሪዎች የነጻ ህክምና አገልግሎት እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ያገኙ ሲሆን በሁለቱ ወረዳዎች ለሚገኙት ማለትም ለሀቼ እና ለሀጤሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የስኳር በሽታና የደም ግፊት መመርመሪያ መሳሪያ ከኮሌጁ እንደተበረከተላቸው ገልጸው ከችግሩ አሳሳቢነት ጋር ተያይዞ ሥራው የሚቀጥልና በወረዳዎቹም "Grand Thematic Project" ለመተግበር ከዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎችና የበላይ አመራሮች ጋር እየተጠናና እየተሰራ በመሆኑ ሲያልቅ በተቀናጀ መልኩ ለ5 ዓመት ለመተግበር ታቅዷል ብለዋል፡፡

የህብረተሰብ ጤና ባለሙያና የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት አስተባባሪ ረ/ፕ ደሳለኝ ጸጋው  እንደተናገሩት ቀደም ባሉት ጊዚያት ትኩረት ሳይሰጣቸው ነገር ግን አሁን በጥናት ሲፈተሽ እነዚህ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች አሳሳቢ እየሆኑ በመምጣታቸው ለህረተሰባችን በነፃ ያሉበት ድረስ በመሄድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት፣ ምርመራና ልየታ እያደረግን ሲሆን ህብረተሰባችንም እነዚህ በሽታዎች ምልክታቸው በጉልህ የሚታየው ከበድ ያለ ደረጃ ላይ ሲደርሱ በመሆኑ አሳሳቢ ደረጃ ሳይደርሱ በአካባቢያቸው ባሉት የጤና ተቋማት በየጊዜው በመሄድ ሊመረመሩና በሐኪሞች የሚሰጧቸውንም ምክርና መድሃኒቶች በአግባቡ መከታተል እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

በሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የውስጥ ደዌ ጠቅላላ ሐኪም የሆኑት ዶ/ር ዘላለም በቀለ እንደገለጹትም በሽታዎቹ ከአኗኗር ዘይቤ፣ ከምግብ አጠቃቀም፣ በቂ የሰውነት እንቅስቃሴ ካለማድረግ እና የሕክምና ክትትል ካለማድረግ ይመጣሉ፡፡





# የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የጆርናል ስርዓት መተግበሪያ ሶፍትዌር ይፋ አደረገ

በስለሺ ነጋሽ



የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕ/ጽ/ቤት በአይ.ሲ.ቲ ዳይሬክቶሬት በኩል ጆርናሎች የሚውል አዲስ የኦንላየን መተግበሪያ ሶፍትዌር ይፋ አድርጓል፡፡ ሶፍትዌሩ ከዚህ ቀደም ለነበሩት 2 ጆርናሎች እና አዳዲስ ለሚመሰረቱት 8 ጆርናሎች የሚውል መሆኑም ተገልጾአል፡፡

የአይ. ኤስ.ቲ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ እሱባለው ገ/ማርያም ሲናገሩ ይሄንን መተግበሪያ ባለሙያዎችን በማቀናጀት የዓለም አቀፍ ጆርናል መተግበሪያ ምን እንደሚመስልና ምን ማሟላት እንዳለበት በመምከር ያዘጋጀን ሲሆን መተግበሪያው ለዩኒቨርሲቲያችን በሚመች መልኩ የተሰራ ነው ብለዋል፡፡

የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ታፈሰ ማቲዎስ ዩኒቨርሲቲው ረጅም የሚባል ልምድ ያለው ሲሆን በእነዚህ ዓመታትም በርካታ ምርምሮችን እያደረገ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እያደረገ ቢሆንም የጆርናሎቹ መጠን ሁለት ብቻ በመሆናቸው ለዩኒቨርሲቲው በቂ ስላልሆኑና በኢትዮጵያ ውስጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ተብለው ከተመረጡት አንዱ በመሆኑ ምርምሮች ላይ ትኩረት ሰጥተን ለምንሰራቸው ስራዎች እንዲረዳን የምርምር ጆርናሎችን መጨመር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ስምንት ተጨማሪ የምርምር ጆርናሎች ተመስርተዋል ብለዋል፡፡ አክለውም እነዚህ የምርምር ጆርናሎችም ተደራሽ እንዲሆኑና ተመራማሪዎችም የሰሯቸውን የምርምር ውጤቶች አሳትመው እንዲያሰራጩ አሁን ባለንበት ዘመን ጊዜው የሚፈልገውን ኦንላየን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የተዘጋጁትን መተግበሪያዎች ተግባራዊ በማድረግ ቀጣይነትና ጥራት እንዲኖራቸው በርትተን መስራት ይኖርብናል ብለዋል፡፡

በዕለቱ የማስጀመሪያ ፕሮግራም ላይ ከዚህ በፊት የአይ.ሲ.ቲ ዳይሬክቶሬት ሰርቶ ተግባራዊ ስላደረጋቸው የተለያዩ ችግር ፈቺ መተግበሪያዎች እና ስለ አዲሱ የኦንላየን ጆርናል ስርዓት መተግበሪያው ዙሪያ በባለሞያዎች ገለጻ ከተደረገ በኃላ በቀረበው የሶፍትዌር መተግበሪያ ላይ ከተሳታፊዎች ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም በስራው ላይ ለተሳተፉ ባለሞያዎች የምስክር ወረቀት በመስጠት የእለቱ ፕሮግራም ተጠናቋል፡፡



# የተፈጥሮና ኮምፒቲሽናል ሳይንስ ኮሌጅ ሁለተኛውን ሀገር አቀፍ የምርምር ኮንፈረንስ አካሄደ

በተስፋዬ ተ/ማ (ኤዲትንግ በሕግኮዳ)





በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ እና ኮምፒቲሽናል ሳይንስ ኮሌጅ ዲን ዶ/ር ዘይቱ ጋሻው ንግግር ባደረጉበት ወቅት "ሳይንሳዊ ምርምር ለዘላቂ ዕድገት፣ አረንጓዴ ቴክኖሎጂ እና የዳታ አብዮት" በሚል ጭብጥ እየተካሄደ ያለውን ኮንፈረንስ አስፈላጊነት ሲገልጹ አካባቢ እና የተፈጥሮ ሀብት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በእጅጉ አስፈላጊዎች መሆናቸው በመገንዘብ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተሰሩ በርካታ ስራዎች የምግብ ምርትን በብዙ እጥፍ ማሳደግ መቻሉን አስረድተው ለስኬቱ የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑ አዳዲስ ዝርያዎች፣ የመንግስት ፖሊሲ ማሻሻያዎች እና ተጨማሪ በጀት መመደቡን እንደ ምክንያትነት አቅርበዋል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር አያኖ ባራሶ በበኩላቸው አካባቢ እና የምግብ ዋስትና ለዘላቂ ልማት ዋነኞቹ ምሶሶዎች መሆናቸውን ጠቅሰው እ.ኤ.አ በ2020 በዓለም አቀፉ የምግብ ዋስትና ግምገማ ሪፖርት መሰረት መካከለኛ እና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው 76 ሀገራት የምግብ ዋስትናን ያላረጋገጡ ሰዎች ቁጥር 844 ሚሊየን መሆኑ ሲጠቀስ በሀገራችን ኢትዮጲያም 20 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ የምግብ ዋስትናውን እንዳላረጋገጠ መጠቀሱን አንስተው ይህ እንደኛ አብዛኛው ህዝብ አርሶአደር በሆነበት ሀገር የችግሩን አሳሳቢነት ከፍተኛ ስለሚያደርገው እንደዛሬ ባሉ ኮንፍረንሶች ላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመራማሪዎች የሚያቀርቧቸው የምርምር ፕሮጀክቶች እና የትግበራ እቅዶች አይተኬ ሚና እንደሚኖራቸው ተናግረዋል፡፡

ከምርምር ጥናት አቅራቢዎች መካከል አንዱ የሆኑት በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ጂኦ ፊዚክስ፣ ህዋ ሳይንስ እና አስትሮኖሚ ተቋም ዳይሬክተሩ ፕ/ር አታላይ አየለ ጥናታቸውን ባቀረቡበት ወቅት እንደተናገሩት ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ በሳይንስ ላይ የተመሰረቱ ምርምሮችን ማካሄድ እና ግኝቶችን በጋራ መገምገም እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

በኮንፈረንሱ ላይ በርካታ ፅሁፎች የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ስለ ታላቁ የኢትዮጲያ ህዳሴ ግድብ የፕሮጀክት ምርምር ሂደቶች እና በኢትዮጲያ ስምጥ ሸለቆ ላይ ስላለው የእሳተ ገሞራ ስጋት የቀረቡት ጥናቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በዕለቱም በነበረው ውይይት በርካታ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች የተሰነዘሩ ሲሆን ከደ/ብ/ብ/ክ እና ሲዳማ ክልል የተውጣጡ ተወካዮች፣ በርካታ ተመራማሪዎች እና ባለድርሻ አካላት ተሳታፊዎች እንደነበሩ ታውቋል፡፡





# በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የወንዶ ገነት ደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ ሶስት የ3ኛ ድግሪ ፕሮግራሞችን ለመክፈት በባለሙያዎች አስገመገመ

በስለሺ ነጋሽ





ኮሌጁ **በደን አያያዝ፣ በደን ስነ–ምህዳር ጥናትና ሲልቪካልቸር** እና **በዱር ህይወት ስነ–ምህዳር** ዙሪያ የ3ኛ ድግሪ ፕሮግራሞችን ለመክፈት ውጫዊ ግምገማ አስደርጓል፡፡

የኮሌጁ ዲን ዶ/ር ሞቱማ ቶሌራ በመክፈቻ ንግግራቸው ኮሌጁ ከ40 በላይ በደንና ተፈጥሮ ሃብት ዙሪያ በመማር ማስተማር፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ላይ በርካታ ስራዎችን በመስራቱ እንደ ሀገር በዘርፉ የልዕቀት ማዕከል መሆኑን ገልጸው ሃገራችን የአረንጓዴ ልማት አሻራ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች በመሆኑ ይሄንንም በእውቀትና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለመምራትና ለማስቀጠል የተማረ ኃይል ስለሚያስፈልግ እነዚህን ፕሮግራሞች መክፈቱ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

በኮሌጁ መምህርና ተመራማሪ ዶ/ር መሰለ ነጋሽ ፕሮግራሞቹ ሀገሪቱ ከያዘቻው አቅጣጫ ጋር የሚያያዙ በመሆኑ እንዲሁም ደንን በዘላቂ ሁኔታ ለመጠቀም፣ ያለንን የደን ሀብታችንንና በውስጡ የሚገኙትን የዱር እንስሳዎችን ለማወቅ እና የደንን መመናመንን እና ውድመትን ለመታደግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ለመስራት በዘርፉ የተማረ የሰው ኃይል ማፍራት ጠቃሚ መሆኑን ተናግረው የሶስተኛ ድግሪ ተማሪዎች ምርምር ላይ ስለሚያተኩሩ ችግሮችን በመለየት ወደ መፍትሄዎቻቸው ለመምጣት እና ለፖሊሲ አዘጋጆች ትልቅ ግብዓት ከመፍጠሩም በተጨማሪ የአረንጓዴ አሻራን ለማስቀጠል ለሀገሪቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ተናግረዋል፡፡



# የትምህርት ኮሌጅ የ2013 ዓ.ም ዕጩ ሴት መምህራን ከአንጋፋ ሴት መምህራን ጋር የልምድ ልውውጥ እንዲያደረጉ የምክክር መድረክ አዘጋጀ

በስለሺ ነጋሽ




የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ኮሌጅ አዲስ የተቀጠሩ የኮሌጁ ሴት ዕጩ መምህራንና አንጋፋ ሴት መምህራን በህይወት ክህሎት ዙሪያ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ መድረክ ያዘጋጀ ሲሆን የኮሌጁ ዲን ዶ/ር አብርሃም ቱሉ በመክፈቻው ላይ ዩኒቨርሲቲው በሀገሪቱ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ተብለው ከተለዩት ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ እንዲሆን የትምህርት ኮሌጅ በመማር ማስተማር፣ በምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎት እና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት እንዲሁም የትምህርት የልህቀት ማዕከል በመሆን ጭምር በርካታ ስራዎችን እየሰራ መሆኑን ገልጸው የመድረኩ ዓላማ በኮሌጁ ራሳችሁን በማሳደግ በመማር ማስተማሩ፣ በምርምር እና በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ያላችሁ አንጋፋ ሴት መምህራን አዲስ ለተቀጠሩት ሴት ዕጩ መምህራን በህይወት ክህሎት ዙሪያ ልምዳችሁን በማካፈል ብቁ እንዲሆኑ እንድትረዷቸው ነው ብለዋል፡፡

ስልጠናውን የሰጡት የሴቶች ህጻናት ወጣቶችና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ምህረት ገነነ በየዓመቱ ለሚቀጠሩት አዲስ ዕጩ መምህራንን ለማብቃት ከኮሌጁ ጋር በጋራ እየሰራን በመሆኑ መልካም አጋጣሚና እድሉን እንድንጠቀም ያስቻለን ሲሆን ማህበረሰቡ ለጾታ በሚሰጠው ትርጉም፣ ሙያ፣ ክህሎት እነዲሁም ተደራራቢ ኃላፊነት የሴቶች ሚና ትርጉሙን አጥቷል ብለዋል፡፡



# የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሲዳማ ጥናት ተቋም በሀገር በቀል ዕውቀቶች ላይ ሲያደርግ በነበረው ምርምር ዙሪያ የምክክር መድረክ አዘጋጀ

በሕግኮዳ





የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር አያኖ ባራሶ ከሲዳማ ክልል፣ ከሀዋሳ ከተማ አስተዳደር እና ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ለተጋበዙ ተሳታፊዎች ንግግር ያደረጉ ሲሆን ኢትዮጵያ በሀገር በቀል ዕዉቀቶች የታደለች ብትሆንም ይህን እውቀት በአግባቡ በመጠቀም ረገድ ከፍተኛ ክፍተት እንደነበር ገልጸዋል:: ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት እኚህን ውድ የሆኑ የሀገር በቀል ዕውቀቶችን በሳይንሳዊ ምርምሮች በመደገፍ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እየተሰራ እንደሚገኝ እና በዚሁ ረገድ ዩኒቨርስቲው ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ምርምሮችን ሲያካሂድ መቆየቱን አብራርተዋል:: እስከ አሁን ባለው ሂደትም በአቅራቢያው በሚገኘው የሲዳማ ክልል ትኩረቱን በማድረግ ጥናቶችን ማካሄዱን አንስተው ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይገደብ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎችም ተንቀሳቅሶ ለመስራት በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል::

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ምር/ቴክ/ሽግ/ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ታፈሰ ማቲዎስ በበኩላቸው እንደ ሀገር  በርካታ ችግር ፈቺ የሆኑ የሀገር በቀል እውቀቶች ቢኖሩንም በህብረተሰቡ ዘንድ በነበረው የአመለካከት ችግሮችና ቀደም ሲል የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ ስላልነበር በዘርፉ ተጠቃሚ ሳንሆን ቆይተናል ብለው በአሁኑ ወቅት እንደ አዲስ በተነደፈው የእድገት ፍኖተ ካርታ መሰረት ለሀገር በቀል ዕውቀቶች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ ዩኒቨርሲቲዎች ምርምሮችን እና ጥናቶችን እያደረጉ እንደሚገኙ ገልጸዋል::

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሲዳማ ጥናት ተቋም ዳይሬክተር የነበሩ ዶ/ር ሳሙኤል ጂሎ ተቋሙ በሲዳማ ህዝብ ባህል፣ ቋንቋ፣ ባህላዊ ህክምና እና የግጭት አፈታት ዘዴዎች ላይ ምርምር ማካሄዱንና በዚህ ምክክር ዝግጅት ላይም በምርምሩ ወቅት የተገኙ ውጤቶች እንደሚቀርቡና እንደሚተቹ እንዲሁም የተቋሙ የወደፊት የጥናትና ምርምር ትኩረት አቅጣጫዎችን በተመለከተ ግብዓቶች እንደሚሰበሰቡ አብራርተዋል::



# የማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ የጥራት ማረጋገጫ መሰረታዊን እና ፕሮግራም ምዘና ላይ ስልጠና ሰጠ

በስለሺ ነጋሽ



በስልጠናው  መክፈቻ ላይ ንግግር ያደረጉት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍስሃ ጌታቸው እንደ ዩኒቨርሲቲ ፕሮግራሞችን ከማስፋፋትና ምርምሮችን ከማድረግ አኳያ ጠቃሚ የሆኑትን በመለየትና ጥራቶቹን በመለካት ለወደፊትም በጥራት ዙሪያ በርትተን ልንሰራ የሚገባን ጉዳይ ነው ብለዋል፡፡ አክለውም በሚቀጥሉት ዓመታት ፕሮግራሞችን መክፈት የምንችለው ከሀገር አቀፍ ጥራትና ምዘና ዕውቅና ሲሰጠን በመሆኑ ብቃት ያላቸውን መምህራንን በመቅጠርና በማሰልጠን ልንዘጋጅ ይገባል ብለዋል፡፡

የማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ ዲን ዶ/ር ዳኜ ሽብሩ በበኩላቸው ትምህርትን ከማስፋፋት አኳያ እየተሰራ ያለው ነገር ጥሩ ቢሆንም የጥራት ጉዳይ ክፍተት የሚታይበት በመሆኑ የትምህርትን ጥራት ለማስጠበቅ በርትተን ልንሰራበት ይገባል ብለዋል፡፡

በፕሮግራሙም ላይ በጥራት ማረጋገጫ መሰረታዊያን፣ ዓላማ እና የትምህርት ፕሮግራሞች እንዴት እንደሚመዘኑ በምሁራን ቀርቦ በተሳታፊዎች ጥያቄዎችና ውይይት ከተካሄደ በኋላ ፕሮግራሙ ተጠናቋል፡፡



# ስራ አጥ ወጣቶች ተደራጅተው በዶሮ እርባታ ስራዎች እንዲሰማሩ ተደረገ

በስለሺ ነጋሽ



በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ምር/ቴ/ሽ/ም/ፕሬ/ጽ/ቤት ስር የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ከሀዋሳና ለኩ ከተማ አስተዳደሮች ጋር በመተባበር ስራ-አጥ ወጣቶችን በማህበር በማደራጀት በዶሮ እርባታ ላይ እንዲሰማሩ የተደረገበትን እንቅስቃሴ በሚመለከት በለኩ ከተማ የመስክ ምልከታ ተደርጓል፡፡

ም/ፕሬዝዳንቱ ዶ/ር ታፈሰ ማቲዮስ ዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት በሰባት ዘርፎች ማለትም በሰብል ምርት፣ በእንስሳት እርባታ፣ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ፣ በትምህርት፣ በጤናና ስነምግብ፣ ነጻ የህግ አገልግሎትና በተለያዩ የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በዩኒቨርሲቲው አጎራባች በሚገኙ በሲዳማ፣ በደቡብና በኦሮሚያ ክልል ወረዳዎች እየሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር አያኖ በራሶ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው ከ1.2 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ በሀዋሳ ከተማ ሶስት እንዲሁም በለኩ ከተማ ሶስት በድምሩ ስድስት በማህበር ለተደራጁ 67 ስራ አጥ ወጣቶች የስራ እድል መፍጠር መቻሉን ገልጸአል፡፡

የሲዳማ ክልል የስራ ዕድል ፈጠራ፣ ኢን/እንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ከፍያለው ከበደ ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ወረዳዎች በምርምር የተደገፉ የማህበረሰብ አገልግሎትና የስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎችን እየሰራ በመሆኑ አመስግነዋል፡፡





# ክብርት ዶ/ር ሂሩት ካሳው በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ችግኝ ተከላ አካሄዱ

በሕግኮዳ



የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር የነበሩ ክብርት ዶ/ር ሂሩት ካሳው እና ከፍተኛ አመራሮች በዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ተገኝተው ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጋር አረንጓዴ አሻራን ለማስቀጠል የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር አካሂደዋል፡፡ ይህ ኢትዮጵያ ከያዘችው ዋነኛውና ቀዳሚው የልማት አቅጣጫ መሆኑን ጠቁመው ለይስሙላ ሳይሆን የትውልድን ህይወት ለማዳን በቁርጠኝነት መሠራት ያለበት ሥራ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲም በመገኘት አሻራቸውን በዚህ መልኩ በማኖራቸው ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማቸው ገልጸዋል፡፡







# የሰላም ሚኒስቴር የብሔራዊ የበጎ ፈቃድ ማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራም ሂደት ስኬትን በማስመልከት የዕውቅና አሰጣጥ መድረክ አዘጋጀ



የሰላም ሚኒስቴሩ "በጎነት ለአብሮነት" በሚልመሪ ቃል ትውልድን የመገንባት ዓላማ ሰንቆ ዩኒቨርሲቲዎችንና መላውን ህብረተሰብ በማነቀሳቀስ ሲያስባብር የቆየ ሲሆን ለዚህ ፕሮግራም መሳካት አስተዋፅዖ ላደረጉ አባላት የምስጋና መርሀ ግብር ማዘጋጀቱ ታውቋል፡፡

በዚህም ሥነሥርዓት ላይ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የብሔራዊ የበጎ ፈቃድ ማህበረሰብ አገልግሎት ወጣቶችን በመቀበልና ስልጠናውን በማመቻቸት ለፕሮግራሙ መሳካት ላደረገው አስተዋፅዖ በሰላም ሚኒስቴር የክብር ተሸላሚ ሆኗል፡፡



# College of Law and Governance Hosts National Research Conference

by Sileshi Negash




College of Law and Governance at Hawassa University organized a National Research Conference on the theme of Governance, Peace, and Justice for sustainable Development of Ethiopia. Dr. Deberework Debebe, Dean of the College of Law and Governance, welcomed the participants and notified them that the researchers were going to present 16 different research papers at the conference. He stated that the conference might provide a special opportunity for researchers and stakeholders of the governmental and non-governmental organizations to exchange experiences, gain new knowledge, and strengthen working relationships in enhancing collaborative efforts.

Dr. Ayele Hagena, a United Nations Environmental Programme Montevideo Environmental Law Programme National Focal Point says that the principle of sustainable development is embedded with the idea of long-term common interest controlling the treats of natural resources by humans. He strongly suggests that their utilization should have limitations to ensure their sustainability. The Law and Governance College is a key knowledge hub potential in a university to transform existing Governance, Peace, and Justice Problems. With their local reach and relevant skills and capacities, the governance and law schools are a real asset that fosters law development, compliance, and enforcement.

Dr. Demeke Achiso, from the Department of Political Science and International Relations in Addis Ababa University, presents a keynote speech and declares that the conference reflects the presence of vested interest and inquisitiveness on the part of the University scholars and concerned institutions to come together. It also brings all interested stakeholders together to exchange their experiences and views and to handle prevailing complex national socio-political situations in a collaborative, comprehensive, and integrative manner.





Hawassa University hosts Ethiopian Premier League Matches, BETKING, in its Main Campus Stadium

# Institute of Technology hosts a Third National Conference on Aspiring the Future in Engineering and Technology

By Sileshi Negash





During the opening speech on 7th May 2021, Hawassa University President Dr. Ayano Berasso articulated that the new national science policy and strategy of the country had clearly shown the importance of conducting scientific knowledge production at higher education institutions, among others, and developing science culture. According to his saying, in the community, to pave the avenue towards meeting the goals of development and prosperity of the country at large, the role of a scientific gathering like this conference is significant in many aspects and it helps to achieve this vital national goal as well. He added that it would be his trust that the research conference creates, on one hand, an opportunity for different parties to observe the different research works conducted at a national level in solving the problems of humanity and, on the other hand, a platform for learning from others.

A Scientific Director of the Institute, Dr.Fasika Bete, during his welcoming speech, said, “We are now living in a much smaller world with interconnected information and communications technology, myriad of networks, including the internet, which is, changing the face of business in the world.” He further added, “In this respect, our country is expecting a lot from us and this conference is just beginning for finding solutions for our challenges. It is not going to be easy to sort out a large amount of technological development coming onward, but one thing is for sure: The pace is growing a lot faster and we are expected more comprehensive, thematic based researches, technology transfers, and better community services and we need to work to a better quality of life for us and society at large.”

The theme of the conference was on the subject of Aspiring the Future in Engineering and Technology and the researchers from the Ethiopian universities and abroad diversely presented their researches output in the theme boundary. Finally, the participants made a crucial discussion around the presented issues and forwarded constructive ideas.



# Hawassa University Goes into a Memorandum of Understanding with NGDO Catalan Association forCooperation Sport Development and Education

By Sileshi Negash



On behalf of Hawassa University and acting as Representative of President of Hawassa University, Dr. Eng. Fisiha Getachew (PhD), has welcomed all, for a cooperation program between Hawassa University and NGDO Catalan Association for Cooperation, Sport, Development, and Education (ACCeDE). He has forwarded his thanksgiving to Hawassa University President Dr. Ayano Berasso and ACCeDE for giving duly attention to organizing this cooperation program.

Dr. Eng. Fisiha mentioned that the aim of ACCeDE is consistent with the works of Hawassa University since both have an aim to promote education through sport as an element of the development of the education and particularly facilitating access to the practice of sport to citizens at the youngest ages.

Nextly, D. Xavier Esteban Martín, acting under his appointment as President, made a presentation, in the name and on behalf of ACCeDE, to invited persons from Hawassa University and others.

Finally, both ACCeDE and Hawassa University signed an MOU agreement for establishing a mutual collaboration to promote education through sport.



# Hawassa University Hosts National Conference on Enhancing Reading Culture for Quality Education and Research

By Sileshi Negash




The Institute of Policy and Development Research (IPDR) and Library and Documentation Services Directorate (LDSD), in collaboration with the Vice President for Research and Technology Transfer (VPRTT), organize National Conference on the theme '*Enhancing Reading Culture for Quality Education and Research*'.

Prof. Tesfaye Semela, IPDR Director and Chairperson of the organizing committee, pointed out a commitment to relevant and quality education is a commitment to human dignity. Equipping the future generation with foundational literacy skills takes a central place in paving the way for the country to plan, finance, and implement solutions to its development challenges.

Dr. Tafese Matiwos, VPRTT, noted that Hawassa University as one of the pioneering higher learning institutions in Ethiopia is mandated to provide quality education, carry out relevant problem-solving research, and engage in community services provision.

Dr. Fiseha Getachew, Vice President for Academic Affairs, also declared that currently as depicted in our 10 years strategic plan we gave more attention to program relevance, and priority is given to enhance quality education and research.

As a keynote speaker, Prof. Darge Wole, from Addis Ababa University, presented and shared his experiences and knowledge vastly on the issue. Different researchers presented their researches and the participants made valuable discussions under the raised issues in the presentations.





# College of Natural and Computational Science Hosts Third National Research Conference

By Sileshi Negash





Hawassa University College of Natural and Computational Science held third national research conference under the theme '*Bringing Products of Nature and Services to the Public: Medicinal Plants, Indigenous Knowledge and Practice*'. Dr. Zeytu Gashaw, Dean, College of Natural and Computational Science, explained that nature has provided a human being with rich botanical wealth and large number of diverse plant species. Biodiversity, in other words, is the gift of nature to plant earth. Therefore, we have to focus on how to play a great role in investigating the mysterious of the nature with support of technology this time.

Dr. Ayano Berasso, Hawassa University President, stated that medicinal plants as a part of plant biodiversity are abundantly distributed in different ecological situations in developing countries. Traditional medicine practitioners mostly implement herbs, spiritual healing, bone-setting, and minor surgical procedures in treating diseases. Ethiopia's traditional medicine is vastly complex, diverse, and varies greatly among ethnic groups. The country is an important regional center for biological diversity due to its suitable geographical land.

There were presentations on different areas of the same theme during the conference. Prof. Ermias Dagne, Emeritus Professor of Chemistry at Addis Ababa University, made very impressive presentation on developing products of nature for health, body care, economic benefits, and how to bring natural products to the public. While Mrs. Abebech Shiferaw presented on traditional plants and her age-long experiences, Dr. Frew Kebede, Associate Professor of Botany at Hawassa University, presented on medical plants of Ethiopia focusing on the use and conservation status.





# College of Agriculture Conducts Internal Curriculum Review Workshop

By Mathewos W.Giorgis



Hawassa University College of Agriculture organized the workshop to make an internal review on the developed curricula under the school of animal and range sciences and faculty of environment, gender, and development studies. The curriculum review workshop opened on 26th June 2021 to evaluate the curricula of the four Ph.D. programs (PhD in Livestock Science and Production, PhD in Agricultural Economics, PhD in Dairy Science and Technology, and PhD in Animal Biotechnology) at an internal level. With regard to this, the significant contribution and great role of the School Directors (Dr. Sintayehu Yigrem, Director, School of Animal and Range Sciences; Mr. Zerihun Ganewo, Director, Faculty of Gender, Environment and Development Studies) are highly appreciated.

Dr. Tarekegn Yoseph, Dean, College of Agriculture, welcomed the speaker of the day, distinguished guests, and other participants following the introduction part. As his explanation, training the competent, efficient, and skilled personnel capable of transforming the existing Livestock and Agricultural Resources into a vibrant economic system is very important to strengthen the sector of agriculture constrained by several factors visible at the country level. Therefore, according to him, these programs play their role in contributing the knowledge-, skill-, and attitude-targeted competencies that enable graduates who will train under these programs.

Dr. Eng. Fisseha Getachew, Vice President for Academic Affairs at Hawassa University, made an opening speech and explained the importance of the curricula review in the area. It is a necessary step at a university level to broaden research areas since Hawassa University is differentiated as a research university, and at the country level to contribute much to economic development.

The presenters, in their turn, emphasized the background and rationale of each program, justifications for its launching, objectives to attain at the end, and professional profiles expected after completion of each program. Finally, the participants were actively involved in suggesting and forwarding priceless comments during the discussion session.

# Hawassa University, Indian Embassy in Collaboration Celebrate International Yoga Day at Hawassa University

By Sileshi Negash






Dr. R. Karunakaran, an Associate Professor at Hawassa University, introduced the program to the participants and Dr. Eng. Fiseha Getachew, Vice President for Academic Affairs at Hawassa University, officially opened the program and welcomed participants.

Dr. Eng. Fiseha Getachew forwarded his thanks to the Indian Embassy and the Indian Council of Cultural Relations, New Delhi mentioning that he understands that ICCR is organizing several cultural events to strengthen bilateral relationships between India and Ethiopia. The present Yoga Celebration is one in the series, and it is being celebrated on June 21st every year. In addition to that, he said that we consider this as a great opportunity to know about Yoga as one of the significant health care systems. UN has recognized this practice as Yoga has proved to be one of the best means to keep one's body and mind under healthy conditions.

Dr. Eng. Fiseha further mentioned that Yoga is an invaluable gift of ancient Indian tradition. It embodies unity of mind and body. It represents thought and action. Yoga is not merely to do exercises but to discover the sense of one's with us. Yoga controls emotional activities and brings harmony to all walks of life. Doing yoga can prevent and cure diseases. Yoga can promote health. Yoga practices aim to overcome all kinds of suffering and stress in life. Thereby it will lead to a life with good health happiness and harmony.

On behalf of Hawassa University, Dr. Eng. Fiseha Getachew has forwarded indeed thankful to Indian Embassy for having given this wonderful opportunity to host this International event at Hawassa University. He stated that Indian Embassy is always supporting Universities in Ethiopia in diverse fields. Besides Business Forum, Indian Embassy has also established Indian Educational Forum to strengthen Education in Ethiopia. The bondage between India and Ethiopia is more than 70 years. During this period the cultural connections established between these two countries were intensified. Most of the Indian Teachers who worked in Schools in Ethiopia are still remembered for their excellent contribution to education in Ethiopia, and still, they were the role models for the present-day teachers in Ethiopia.

Crucially, Dr. Fesiha stated that the Ethiopian Academicians regularly witnessing the activities of ICCR through the '*India in Ethiopia Website*' The publication titled India Ethiopia 70 years of Diplomatic Relations reveals several interesting facts. There are strong bonds between India-Ethiopia co-operations in the field of education.

Yoga Demonstration has been done by Dr. M.Jeevanandam, an Assistant Professor, from Department of Geology at Hawassa University.

